38725.doc

38741.doc

38745.doc

38776.doc

38935.doc

39175.doc

39485.doc

39579.doc

34540.doc

35689.doc

36040.doc

36460.doc

36756.doc

37503.doc

37894.doc

38041.doc

38126.doc

https://chilot.me

የሰበር መ/ቁ. 38725

24/07/2001

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡-የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ፍ/ሕ ቢሮ - ዐቃቤ ሕግ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- እነ ጃምቦ ጃርሶ /5 ሰዎች/ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ለደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር አቤቱታ አቅርቦ ጉዳዩን አልተከታተለም ተብሎ መዝገቡ በመዘጋቱ ምክንያት ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ሲታይ ተጠሪዎች በግብረአበርነት የሰው መግደል ወንጀል ፈጽመዋል በማለት አመልካች በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት በጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት የወንጀል ክስ መሥርቶባቸው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ ተጠሪዎች ጥፋተኛ ናቸው ብሎ 1ኛ፣3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎችን በእድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ሲቀጣ 2ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች አያንዳንዳቸው በ15 ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጡ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተከሣሾች በዚሁ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ይግባኝ ባዮች ላይ

የተሰጠው የጥፋተኛነት ውሣኔ በቂ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ ነው በማለት የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሣኔ ሽሮ በነፃ እንዲለቀቁ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ከሣሽም ይህ ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም አቤቱታው ያስቀርባል አያስቀርብም የሚለውን ትእዛዝ ከመስጠቱ በፊት የፖሊስ የምርመራ መዝገብ እንዲቀርብ ትእዛዝ መስጠቱን ከመዝገቡ ግልባጭ የተረዳን ሲሆን ነገር ግን ተፈላጊው የፖሊስ የምርመራ መዝገብ እንዲቀረብ የተደጋገመ ትእዛዝ ተሰጥቶ ባለመቅረቡና አመልካች ዐቃቤ ሕግም ጉዳዩን አልተከታተለም በሚል ፍ/ቤቱ መዝገቡን መዝጋቱንም ተገንዝበናል፡፡

ከዚህ በኋላም አመልካች በ21/5/2000 ዓ.ም በዋለው ቀጠሮ መዝገቡ ሊዘጋ የቻለው ቀጠሮውን ባለማወቃችን ስለሆነ የተዘጋው መዝገብ እንዲከፈት ይታዘዝልን በማለት አቤቱታውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቅርቦ ፍ/ቤቱም የፖሊስ ምርመራ መዝገብ እንዲቀርብ ተደጋጋሚ ትእዛዝ መስጠቱንና ይህንንም ትእዛዝ አመልካች መገንዘቡን ለጉዳዩም ተገቢውን ትኩረት እንዳልሰጠ በመጥቀስ የተዘጋው መዝገብ እንዲከፈት የቀረበው ጥያቄ በተገቢው አይደለም በማለት ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

ለዚህም ችሎት የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይሄው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታው ለሰበር መቅረብ እንዳለበት በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

አመልካች የተዘጋው መዝገብ እንዲከፈት ይታዘዝልኝ በማለት ለደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም መባሉ አግባብነቱ ከሕግ አኳያ ተመርምሯል፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት መዝገቡ እንዲዘጋ ትእዛዝ የሰጠው ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው የፖ/ሊስ የምርመራ መዝገብ እንዲቀርብ የተደጋገመ ትእዛዝ ተሰጥቶ አልቀረበም ዐቃቤ ሕግም ጉዳዩን አልተከታተለም በሚል ነው፡፡

ይሁንና ተፈላጊው የፖ/ሊስ የምርመራ መዝገብ አልቀረበም ቢባልም ሰበር ችሎቱ የተቋቋመው የመጨረሻው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ከሆነ ይህንኑ ለማረም ስለሆነ በዚሁ መሠረት የመጨረሻውን ፍ/ቤት ውሣኔ መርምሮ በሰበር ሊታረም የሚችል የሕግ ስህተት መኖሩን ካመነ አቤቱታው ለሰበር ይቅረብ ብሎ የግራ ቀኙን ክርክር በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 192 መሠረት ለመስማት ቀጠሮ መስጠት ይህም ካልሆነም አቤቱታው ለሰበር የሚያስቀርብ ካልሆነም አይቀርብም ብሎ የሰበር አመልካችን ማሰናበት ሲገባ የምርመራ መዝገቡ አልቀረበም በማለት መዝገቡን መዝጋቱ ከሰበር ችሎት የሕግ አሠራርም ሆነ ከሥነ ሠርዓት ሕጉ አኳያ ተገቢነት የሌለውና የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የደቡብ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 14845 በ5/9/2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የክልሉ ሰበር ችሎት በአመልካች በኩል የቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን እንዲወስን ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰበር /መ/ቁ. 38741

መጋቢት 15 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች ፡- ዳርጌ ተገኝ

ተጠሪዎች ፡- 1. ዳርጌ ተሻለ

2. መንገሻ ተሻለ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤትና ቦታ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ብ/ክ/መ/ በሰሜን ወሎ መስተዳድር ዞን በቆቦ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሣሾች የነበሩት የአሁኖቹ ተጠሪዎች ሲሆኑ፣ በአመልካች እና ወ/ሮ ታየች ተመስገን በተባለች ሰው ላይ ክስ የመሰረቱት የሚች አባታችን አንድ የሣር ክዳን ቤት በአደራ ጠባቂነት እና በጥገኝነት ይዘው ከቆዩ በኋላ አንለቅም ብለውናል፡፡ ከዚህ አልፈውም የሐሰት ሰነድ አዘጋጅተው በማቅረብ አባታችሁ ሸጦልናል ብለውናል፡፡ ስለዚህ በፍርድ ተገደው ቤቱን ያስረክቡን ዘንድ ይወሰንልን በማለት ነው፡፡ ተከሳሾችም ለክሱ በሰጡት መልስ ቤቱን የያዝነው ከከሣሾች አባት እና እናት ጋር የካቲት 15 ቀን 85 ዓ.ም ባደረግነው ውል መሠረት ነው፡፡ ቤቱን ከመግዛታችንም በላይ ለአስራ አምስት /15/ ዓመታት ያክልም በይዞታችን አድርገን

ስንጠቀምበት ቆይተናል፡፡ በማለት ስለመከራከራቸው መዝገቡ የስረዳል፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት ክርክሩን ከሰማ በኋላ ተከሳሾች ቤቱን ለከሣሾች እንዲያስረክቡ የሚገደዱበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት ክሱን ሰርዞአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የስር ከሣሾች በውሣኔው ባለመስማማት ለሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማለታቸው ክርክሩ እንደገና የተሰማ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም የቤት ሽያጭ ውል ተብሎ የቀበውን ሰነድ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1723 እና 2877 የተመለከቱትን መስፈርቶች የማያሟሉ በመሆኑ ፈራሽ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት በወረዳው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን ውሣኔ ሽሮአል፡፡ በመቀጠልም ግራ ቀኝ ተከራካሪ ወገኖች ከውሉ በፊት ወደነበሩት ይመለሱ በማለት የስር ተከሳሾች ቤቱን ለከሣሾች እንዲያስረክቡ ከሣሾች ደግሞ ወላጆቻቸው በቤት ሽያጭ ስም የተቀበሉትን ገንዘብ ለተከሳሾች ይመልሱ በማለት ወስኖአል፡፡ የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤትም በከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ሰኔ 24 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የስር ተከሳሾች አከራካሪውን ቤት ገዝተን ለአስራ አምስት ዓመታት ያክል ይዘነው ቆይተናል በማለት ያቀረቡት ክርክር ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

በክርክሩ እንደተመለከተው ተጠሪዎች ክስ የመሠረቱት የአባታችን ነው የሚሉትን ቤት ለመረከብ ነው፡፡ ከጅምሩ ቤቱ እነሱ የሰሩት ወይም በይዞታቸው

ስር የነበረ አይደለም፡፡ በቤቱ ላይ መብት አለን የሚሉት የአባታችን ወራሾች ነን፡፡ ቤቱም የውርስ ሀብት በመሆኑ ለእኛ ለወራሾች መሰጠት ያለበት ነው ከሚል አስተሳሰብ በመነሳት እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ የስር ተከሳሾች ባቀረቡት ክርክር ደግሞ ቤቱን ከባለንብረቱ ገዝተን ነው የያዝነው ከማለታቸውም በላይ፤ ለአስራ አምስት አመት ያክል በይዞታቸው ስር አድርገው ሲጠቀሙበት እንደቆዩም ገልፀዋል፡፡ በዚህ ክርክራቸውም በከሳሾች እንዲፈፀሙ የተጠየቁትን ግደታ /ቤቱን የማስረከብ ግዴታ/ ይፈጽሙ ዘንድ ሊገደዱ እንደማይገባ በመግለጽ እንደተከራከሩ ነው የሚቆጠረው፡፡ በእርግጥ በሁለቱ መካከል የውል ግንኙነት ባለመኖሩ የስር ተከሳሾች እንዲፈጽሙት የተጠየቁትን ግዴታ (ቤቱን የማሰረከብ ግዴታ) ይፈጽሙ ዘንድ ሊገደዱ እንደማይገባ በመግለጽ እንደተከራከሩ ነው የማቆጠረው፡፡ በእርግጥ በሁለቱ መካከል የውል ግንኙነት ባለመኖሩ የስረ ተከሳሾች እንዲፈጽሙት የተጠየቀው ግዴታ ከውል የመነጨ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ግን የስር ተከሳሾች ክርክር የይርጋ መቃወሚያንም የያዘ በመሆኑ መቃወሚያው ከፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1677/1/ እና 1845 አኳያ መታየት የሚገባው ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1677/1/ እንደተደነገገው ግዴታዎቹ ከውል የተገኙ ባይሆኑም የፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 12 ድንጋጌዎች ይፈጸሙባቸዋል፡፡ በተያዘው ጉዳይ እንዲፈፀም የተጠየቀው ግዴታ የተለየ የይርጋ ደንብ የለውም /ቁ. 1677/2// በመሆኑም አግባብነት ያለት የይርጋ ደንብ በአንቀጽ 12 ስር የሚገኘው ቁ. 1845 ነው፡፡ ይህ ድንጋጌም ግዴታው እንዲፈፀም የሚቀርብ ክስ በአስር ዓመት ይርጋ እንደሚቀር ያመለክታል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ግዴታ እንዲፈጽም /ቤቱን እንዲያስረክብ/ ክስ የቀረበበት ቤቱን ከያዘ ከአስር ዓመት በኋላ ነው በመሆኑም ክሱ በተጠቀሰው ቁ. 1845 በይርጋ ቀሪ ሆኖአል፡፡

የስር ፍ/ቤቶች አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎች ያስረክቡ ዘንድ መወሰናቸው ትክክል አይደለም፡፡ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአማራ ብ/ክ/መ/ የሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር በመ/ቁ. 12352 መጋቢት 19 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 1174/20 ሰኔ 2 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. የስር ተከሳሾችን /አመልካችን/ ነፃ በማድረግ በቆቦ ወረዳ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ በውጤት ደረጃ ፀንቶአል፡፡
3. አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት እንዲያስረክብ አይገደድም፡፡ የቀረበበት ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://chilot.me

የሰበር መ/ቁ. 38745

መጋቢት 10 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

ዓልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ ሳሊያ ኢብራሂም - ወኪል 2ኛ አመልካች

2. አቶ መሐዲን ጀማል ቀርበዋል

ተጠሪ፡- ሐጂ ሰማን ኢሳ- በሌሉበት

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የሚተለውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ክርክር ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች ሰኔ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታቸው የኦሮሚያ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 26/98 ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም እና ሚያዝያ 08 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጣቸው ውሳኔዎች መረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመባቸው በመሆናቸው ይሻሩልን በማለታቸው ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በኢሊባቡር ዞን ከፍተኛ ሸሪዓ ፍ/ቤት ሲሆን በዚሁ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካቾች ተከሳሾች፣የአሁኑ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን የተከራከሩ ሲሆን፣የስር ከሳሹ ነሐሴ 09 ቀን 1998 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት ክስ አጭር ይዘቱ 1ኛዋ ተጠሪ ሚስቱ ሆና እያለች 2ኛው ተጠሪ የሸሪዓን ህግ በመጣስ ስላገባት በጋብቻ ላይ ጋብቻ በመፈፀም ጥፋት ስለፈፀመ በህግ ፊት ቀርቦ የጥፋተኝነት ውሳኔ ይሰጠው የሚል ነው፡፡ ስር ተከሳሾች በቀነ ቀጠሮው ባይቀርቡም የስር ፍ/ቤቱ ሐምሌ 6 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ብይን ጉዳዩ ወንጀል ነክ በመሆኑ አከራካሪ የመወሰን ስልጣን የለኝም በማለት

መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ስር ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪም በስር ፍ/ቤቱ ውሳኔ ላይ ቅሬታ በማሳደር ጉዳዩን በይግባኝ እንዲታይላቸው ለኦሮሚያ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት አቅርበውት ፍ/ቤቱም ተከሳሾቹ በሌሉበት በመ/ቁ 26/98፣ሚያዝያ 08/1999 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ አቶ መሐዲን ጀማል ወ/ሮ ሳሊያ ኢብራሂም የሐጂ ሰማን ኢሳ ህጋዊ ባቤት መሆኗን እያወቀ ስላገባት በጋብቻ ላይ ጋብቻ በመፈፀም ጥፋት ፈጽሟል በማለት ስር ተከሳሾቹ ለከሳሹ ብር 1700 (አንድ ሺህ ሰባት መቶ ብር) እንዲከፍሉትና በሚመለከተው አካል በወንጀል የመክሰስ መብቱ በመጠበቅ ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላም የአሁኑ አመልካቾች ታህሳስ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታቸው ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78/1/2/ መሰረት ባሉበት ክርክሩ እንደገና እንዲካሄድ ፍርዱን ለሰጠው የኦሮሚያ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤት አመልክተው ከተፈቀደላቸው በኋላ ያቀረቡት ክርክር በጋብቻ ላይ ጋብቻ እንዳልፈፀሙ፣አቶ መሐዲን ወ/ሮ ሳሊያን ያገባት ቀደም ብሎ ከሐጂ ሰማን ኢሳ ጋር የነበራትን ጋብቻ /ኒካ ከፈረሰ በኋላ እንደሆነና ማስረጃም እንዳላቸው የሚገልጽ ሲሆን ይግባኝ ባዩ ሐጂ ሰማን ደግሞ ከወ/ሮ ሳሊያ ጋር የነበረኝ ጋብቻ በሸሪዓ ፍ/ቤት አልፈረሰም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤቱም በኦ/ጠ/ሸሪዓ ፍ/ቤት መ/ቁ. 26/98፣ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ ተከሳሾቹ በጋብቻ ላይ ጋብቻ አልፈጸምንም በማለት ያቀረባቸው የጽሁፍ ማስረጃዎች ማለትም የዘመድ ዳኞች በ27/08/1990 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔና የኢልባቦር ዞን የእስልምና ጉዳዮች ጉባኤ በ01/02/1993 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ሲታዩ እነዚህ አካላት ጋብቻውን የማፍረስ ስልጣን የላቸውም በማለት ተከሳሾቹ በጋብቻ ላይ ጋብቻ ፈጽመዋል በማለት ቀደም ብሎ ማለትም በመ/ቁ. 26/98፣ሚያዚያ 08/1999 ዓ.ም ሰጥቶት የነበረውን ውሳኔ ተመልሶ አጽድቆታል፡፡

ከላይ የሰፈረውን ውሳኔ በመቃወምም የአሁኑ አመልካቾች ሰኔ 23 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም በጋብቻ ላይ ጋብቻ

አልፈፀምንም፤ጋብቻችንን የፈጸምነው በ1ኛ አመልካችና በተጠሪው መካከል የነበረው ጋብቻ በህጋዊ አካል ከፈረሰ በኋላና ይህንን መሰረት በማድረግ የኤልባቦር ዞን የእስልምና ጉዳዮች ጉብኤ በቁጥር DHIIL 62/3/3-1/93 ጥቅምት 01/1993 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ ወ/ሮ ሳሊያ ኢብራሂም ጋብቻዋ የፈረሰ በመሆኑ የፈለገችውን ማግባት እንደምትችል ማረጋገጫ ከሰጠ በኋላ እንደሆነ፤በጋብቻ ላይ ጋብቻ ፈጽማችኋል በማለት በብር 1700 (አንድ ሺህ ሰባት መቶ ብር) በወንጀል እንድንቀጣ መወሰኑ መዝገቡን በጥልቀት ሳይመረምር ከስልጣኑ ውጭ እንደሆነ በመግለጽ በኦ/ጠ/ሸሪዓ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ይሻርልን የሚል ነው፡፡

ተጠሪው ለቃል ክርክር ተዘጋጅተው እንዲቀርቡ መጥሪያው ደርሷቸው ባለመቅረባቸው ፍ/ቤቱ ጥር 14 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ አዞ እየተካሄደ ያለ በመሆኑ ተጠሪው መልስ አልሰጡም፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጥ ከላይ እየተዘረዘረ በመጣው መልኩ ከተገነዘበ በኋላ አመልካቾቹ ጋብቻ የፈፀሙት 1ኛዋ አመልካችና ተጠሪው መስርተውት የነበረው ጋብቻ በህጋዊ መንገድ ሳይፈርስ በነበረበት ሁኔታ ነው ወይስ አይደለም? የሚል መሰረታዊ ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ 1ኛዋ ተጠሪ ከእርሳቸው ጋር ያላት ጋብቻ በሸሪዓ ህግ ሳይፈርስ 2ኛው ተጠሪ እንዳገባትና ይህ አድራጐትም በጋብቻ ላይ ጋብቻ መፈጸም ስለሆነ አመልካቾች እንዲቀጡለት የሚጠይቅ ሲሆን አመልካቾቹ ደግሞ ቀደም ብሎ በተጠሪው እና በ1ኛ አመልካች መካከል የነበረው ጋብቻ በአግባቡ ከፈረሰ በኋላ እንጂ ጋብቻው ሳይፈርስ እንዳልተጋቡ መልሰዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያከራከረው የኤልባቦር ዞን ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ጉዳዩ የወንጀል ክርክር ስለሆነ ስልጣን የለኝም ቢልም ጉዳዩን በይግባኝ ያስተናገደው የኦሮሚያ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ግን በ1ኛዋ አመልካችና በተጠሪው መካከል ቀደም ብሎ የተመሰረተው ጋብቻ ፀንቶ

ባለበት ጊዜ 2ኛው ተጠሪ 1ኛዋን ተጠሪ በማግባት በጋብቻ ላይ ጋብቻ መፈፀሙ በማስመር በብር 1700(አንድ ሺህ ሰባት መቶ ብር) እንዲቀጣቸው ነው። ሽማግሌዎች አፋትተውናል ፍርድ ቤትም ተቀብሎታል፣ቀጥሎም የኢልባቦር ዞን የእስልምና ጉዳዮች ጉባኤ 1ኛዋ አመልካች የፈለገችውን ማግባት እንደምትችል በደብዳቤ ገልፆላታል የሚል ክርክር ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ስልጣን የላቸውም በማለት አልፎታል። ይሁን እንጂ ቀደም ብሎ በተጠሪውና በ1ኛዋ አመልካች መካከል የነበረው ጋብቻ እንዲፈርስ ጥያቄ የቀረበለት የዲዱ ላሎ ወረዳ ፍ/ቤት ጉዳዩ ወደ ሽማግሌዎች መርቶት ሽማግሌዎቹ ተጋቢዎቹን ለማስታረቅ ያደረጉት ጥረት ሳይሳካ በመቅረቡ ጋብቻው እንዲፈርስ አስተያየታቸውን ተመልሰው ለወረዳ ፍ/ቤቱ ካቀረቡለት በኋላ የተጠቀሰው ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 48/94፣ሚያዚያ 28 ቀን 1990 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሽማግሌዎቹን አስተያየት ተቀብሎ ፍቺውን እንዳፀደቀ መዝገቡ ያስረዳል፤የመጀመያሪው ጋብቻ የፍቺ ሂደት በዚህ መልክ ከተጠናቀቀ በኋላ እና የኤልባቦር ዞን እስልምና ጉዳዮች ጉባኤ በቁ. DHIILU 62/3/3-1/93 ጥቅምት 01/1993 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ 1ኛዋ አመልካች ከዚህ በኋላ የፈለገችውን ሰው ማግባት እንደምትችል ገልጿል። የአሁኑ 2ኛው አመልካች እነዚህ ሂደቶች ማለትም የመጀመሪያው ጋብቻ ስልጣን ባለው የወረዳ ፍ/ቤቱ አማካኝነት መፍረሱ አረጋግጠው 1ኛዋ አመልካች እንዳገቡ ነው። የእስልምና ተከታይ የሆኑ ተጋቢዎች ጋብቻቸው እንዲፈርስ ወደ መደበኛ ፍ/ቤት ወይም ሁለቱም ከፈቀዱ ደግሞ ወደ ሸሪዓ ፍ/ቤት አስቀርበው እንደምርጫቸው ሊያፈርሱት እንደሚችሉ እየታወቀ የኦሮሚያ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤት የዲዱ ላሎ ወረዳ መደበኛ ፍ/ቤት ቀደም ብሎ የሰጠውን የፍቺ ውሳኔ ወደ ጐን በመተው በ1ኛዋ አመልካችና በተጠሪው መካከል የነበረው ጋብቻ አልፈረሰም፤አመልካቾች በጋብቻ ላይ ጋብቻ ፈጽመዋል ማለቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፤ ስለሆነም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል።

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 26/98፣ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሸሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. አመልካቾቹ ጋብቻ የፈጸሙት ቀደም ብሎ በ1ኛዋ አመልካችና በተጠሪው መካከል የነበረው ጋብቻ በዲዱ ላሎ ወረዳ ፍ/ቤት በአግባቡ ከፈረሰ በኋላ በመሆኑ አመልካቾቹ በጋብቻ ላይ ጋብቻ ባለመፈጸማቸው የተላለፈባቸው የገንዘብ ቅጣት ተገቢ አይደለም ብለናል፡፡
3. ግራና ቀኙ ወገኖች በዚህ ፍ/ቤት ላካሄዱት ክርክር ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. ጥር 14 ቀን 2001 ዓ.ም የተላለፈው እግድ ተነስቷል፤ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ያለቀ በመሆኑ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን

https://chilot.me

የሰበር መ/ቁ 38776

መጋቢት 10 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ አበባ አበበ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- እነ ወ/ሮ አንጓች ዘለቀ - በሌሉበት የሚታይ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በሺያጭ የተላለፈልኝ መኖሪያ ቤት ሥመ ሃብት ይዛወርልኝን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኗ አመልካች ሠኔ 15 ቀን 1999 ዓ.ም በዓፉት የክስ ማመልከቻ በየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 03 ውስጥ የሚገኘውን ቁጥሩ 1471 የሆነውን በካርታ ቁጥር 23385 በ1ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን መኖሪያ ቤት ህዳር 28 ቀን 1979 ዓ.ም በተደረገ የሺያጭ ውል ገዝተው ብር 1600 (አንድ ሺህ ስድስት መቶ ብር) ለሻጮች በመክፈል ቤቱንና ቤቱን የሚመለከቱ ሠነዶችን መረከባቸውን ሆኖም ሻጮች በሙሉ በገቡት ግዴታ ስመ ሀብቱን ማዛወር ሲገባቸው አድራሻቸውን በመሠወር ሊገኙ ባለመቻላቸው አመልካች ክስ እስከመሰረቱበት ጊዜ ግብሩን በ1ኛ ተጠሪ ስም እየገበሩ መሆኑን የክፍሉ መሬት አስተዳደርም ስመ ሃብቱን እንዲያዛውርላቸው አመልካች ቢጠይቁት የተጠሪዎችን መቅረብ አስፈላጊ መሆኑን በመግለጽ የአመልካች ጥያቄ ማስተናገድ አለመቻሉን በመዘርዘር ተጠሪዎች ካሉበት በጋዜጣ ጥሪ

https://chilot.me

ተደርጐላቸው ቀርበው የቤቱን ስመ ሀብት በአመልካች ሥም እንዲያዛውሩ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው በተጠሪዎች ላይ በፌዳራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪዎች ጥሪ ተደርጐላቸው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ታዟል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም በአመልካች በ በኩል የቀረቡትን ማስረጃዎችን መርምሮ የሽያጭ ውሉን በሕግ የሚፀና አለመሆኑን የሰበር ችሎቱ ውሳኔ በዋቢነት በመጥቀስ ተጠሪዎች የቤቱን ስመ ሐብት በአመልካች ስም እንዲያዛውሩ አይገደዱም በማለት ወስኖ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ሠርዞታል የአሁኑ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ በመቃወም ለማሰለወጥ ነው፡፡

አመልካች ሠኔ 26 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል ይዘቱም ባጭሩ የሽያጭ ውሉ ተደርጐ ሙሉ ክፍያውም ተፈጽሞ ካርታ፣ ቤቱ፣ ልዩ ልዩ ሠነዶችን አመልካች በተረከቡበት ሁኔታ ተከራካሪ ባልቀረበበት ጉዳይ ከተጠየቀው ዳኝነት ውጭ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ተሽሮ ተገቢ ውሣኔ ይሠጣቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ ተመርምሮም በሠበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጐላቸው ባለመቅረባቸው ጉዳይ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ዓቢይ ነጥብ ሥም

https://chilot.me

ይዛወርልኝ ተብሎ ለቀረበ የዳኝነት ጥያቄ በህግ ፊት የሚፀና ውል የለም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከመዝገቡ መገንዘብ የተቻለው አመልካች ህዳር 28 ቀን 1979 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል ተላልፎለኛል የሚሉትን የመኖሪያ ቤት ካርታ ልዩ ልዩ ሠነዶች መረከባቸውን ተጠሪዎች ፍ/ቤት ሣይቀርቡ መቅረታቸውን ነው፡፡

አመልካች ከተጠሪዎች ጋር ተደርጓል በሚሉት ስምምነት ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ተረክበው በይዞታቸው ሥር አድርገው እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆኑን ገልፀው በግልጽ የጠየቁት ዳኝነትም የቤቱ ሥመ ሀብት እንዲዛወርላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ነው፡፡ ይህንኑ የዳኝነት ጥያቄ ተጠሪዎች ፍ/ቤት ቀርበው ከሥር ያልተከራከሩበት ሁኖ የስር ፍ/ቤት ግን የሽያጭ ውሉን ፎርማሊቲ በራሱ ጊዜ በማንሣት በሕግ ፊት የሚፀና አይደለም ወደ ሚለው ድምዳሜ ደርሶ ተጠሪዎች ሊገደዱ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ ከዚህ በቀላሉ መገንዘብ የሚቻለው የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ባላገናዘበ መልኩ የተሰጠ ስለመሆኑ ነው፡፡ በመሠረቱ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተከራካሪዎቹ ወገኖች በዝርዝር ባላቀረቡት ወይም በግልጽ ባላመለከቱት ጉዳይ ላይ ፍርድ ለመስጠት የማይችል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 182(2) ሥር ተደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል ስለውሉ ህጋዊነት ክርክር ባልተነሣበት ሁኔታ ፍ/ቤት በራሱ ጊዜ በማንሣት መወሠን የሚችልበት የክርክር አመራር ሥርዓት ስላለመኖሩ አንድ ፍ/ቤት ባለጉዳዮችን የሚያከራክረው ለጉዳዩ አወሣሰን የሚያስፈልገውን ጭብጥ በመያዝ ነው ተብሎ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 246 (1) ከተደነገገው ድንጋጌ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕቁ 247(1) ድንጋጌ ሲታይ ደግሞ ጭብጥ የሚመሠረተው አንደኛው ተከራካሪ ወገን ያመነውን የህግ ወይም የነገር አግባብ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን በማስተባበል የካደ እንደሆነ ስለመሆኑ ያስገነዝባል እንዲሁም ጭብጥ ሊመሠረት

https://chilot.me

የሚችለው ግራ ቀኙ ካቀረባቸው ክርክሮች በመነሣት መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 248 ድንጋጌ ያመለክታል በመሆኑም የሽያጭ ውል በህጉ የተመለከተውን የአፃፃፍ ሥርዓት ባለመከተሉ በሕግ ፊት አይፀናም የሚል ክርክር በስር ፍ/ቤት በተከራካሪ ወገን ባልቀረበበት ሁኔታ ፍ/ቤቱ በራሱ በጭብጥነት ይዞ ውሳኔ መስጠቱ በፍ/ብ/ህግ ሥነ ሥርዓቱ የተመለከተውን የጭብጥ አያያዝና የዳኝነት አሠጣጥ ሥርዓት ባልተከተለ መንገድ ነው፡፡

ከላይ እንደተገለፀው የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ የሥመ ንብረት ይዛወርልኝ ሲሆን የስር ፍ/ቤትም የዚህኑ ጥያቄ አግባብነት ለመመርመር ውሣኔ መስጠት ነበረበት ይህ ችሎትም የአመልካችን ጥያቄ ከህጉ ጋር በማገናዘብ እልባት መስጠቱን አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ከአመልካች ክስ እና ክርክር ማረጋገጥ የተቻለው ከተጠሪዎች ጋር በተደረገው ስምምነት መሠረት ቤቱን ካርታውን ሌሎች አስፈላጊ ሠነዶችን ተረክበው በተጠሪዎነች በኩል መፈፀም አለበት የተባለው የቤቱ ሥመ ሀብት ማዞር ብቻ መሆኑን ነው፡፡ ሆኖም የስም ዝውውር ተግባር የሚፈፀመው በመንግሥት አስተዳደር ክፍል ፊት ሲሆን ሻጭ ነው የተባለው ወገን ሊፈጽመው የሚገባ ከህግ ወይም ከውል የሚመነጭ ግዴታ አይደለም የስም ዝውውር ጥያቄ የሚስተናግደው የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት እንዲሠጥ በህጉ ሥልጣን በተሠጠው የመንግሥት አስተዳደር አካል ስለመሆኑ የፍ/ህ/ቁ 1195 ድንጋጌ ይዘት የሚያስገነዝበን ጉዳይ ሲሆን ይህው አካል የስም ዝውውሩን የሚፈጽመው ገዥው ውልና አስፈላጊ ሠነዶችን ይዞ ሲቀርብለት ነው፡፡ በመሆኑም የስም ይዛወርልኝ ጥያቄ በፍ/ቤት ክስ ቀርቦ ዳኝነት የሚሠጥበት ጉዳይ አይደለም ምክንያቱም አንድ ክስ ለፍ/ቤት የሚቀርበው ተከሣሽ ለከሣሽ ሊፈጽመው የሚገባው ግዴታ መኖሩ ሲታወቅ ነውና፡፡ ስለሆነም የስም ይዛወርልኝ ጥያቄም በሻጭ ላይ የሚጥለው የህግም ሆነ የውል ግዴታ ስለሌለ በፍ/ቤት ክስ ቀርቦ ዳኝነት የሚሰጥበት

https://chilot.me

ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 231/1ሀ/ መሠረት ፍሬ ነገሩ የሚያስከስስ ነው ተብሎ መወሰን ያለበት ጉዳይ ነው ይህ ስለመሆኑ ይህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 14222 ትርጓሜ ሠጥቶበታል፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች ተጠሪዎች ተጠርተው ቀርበው የቤቱን ሥመ ሀብት እንዲያዛውሩልኝ ይወሰንልኝ ብለው ዳኝነት መጠየቃቸው በፍ/ቤት ቀርቦ ዳኝነት የሚያሰጥ ጉዳይ በመሆኑ ክሣቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 231 (1ሀ) መሠረት የሚያስከስስ ፍሬ ነገር የለውም ተብሎ ውድቅ መሆን የነበረበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 36554 በቀን 26/05/2000 ዓ.ም ተሰጥቶ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 64433 ግንቦት 25 ቀን 2000 ዓ.ም በትእዛዙ የፀናው ውሣኔ በተለወጠ ምክንያት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት በአብላጫ ድምጽ ፀንቷል
2. አመልካች የስም ይዛወርልኝ ጥያቄ አቅርበው ከተጠየቀው ዳኝነት በተለየ ሁኔታ ውሉ በህግ ፊት የሚፀና አይደለም ተብሎ መወሰኑ የክርክር አመራርንና የዳኝነት አሠጣጥ ሥርዓትን የተከተለ አይደለም ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የአመልካች የስም ይዛወርልኝ ጥያቄ የሚያስከስስ ምክንያት የለውም ብለናል
4. ወጪና ኪሣራ አመልካች የራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://chilot.me

የ ሐ ሳ ብ ል ዩ ነ ት

እኔ ስሜ በአምስተኛው ተራ ቁጥር የተጠቀሰው ዳኛ ከአብላጫው ድምጽ የውሳን መኖርና ህጋዊነት አስመልክቶ የሥር ፍርድ ቤት በራሱ ተነሳሽነት አከራካሪ ያልሆነውን የውል ፎርም ጉዳይ በማንሣት ውሉ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት የሰጠውን ውሣኔ በመሻሩ ሙሉ ለሙሉ እስማማለሁ። ሆኖም አብላጫው ድምጽ አመልካች ያቀረበው የውል ይፈፀምልኝ ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም በማለት በደረሰበት መደምደሚያ በስር መዝገብ ቁጥር 36496 ህዳር 11 ቀን 2001 ዓ.ም አብላጫው ድምጽ በተመሣሣይ ጭብጥ ላይ ውሣኔ ሲሰጥ በዝርዝር በገለጽኩት ምክንያት አሣማኝ ሆኖ አላገኘሁትም። ስለሆነም

- ከውልና ማስረጃ ያልተረጋገጠ ውል የያዘ ገዥ ስመ ንብረቱ በአስተዳደር ክፍል ሊዛወርለት የሚቻለው ፍርድ ቤት ለውሉ መሠረት እንዲፈፀም ሊወሰን ወይም ሻጭ አስተዳደር መሥሪያ ቤት ቀርቦ በስም ማዛወሪያ ቅጽ ላይ ሲፈርም በመሆኑና ተጠሪ ይህንን ለማድረግ ፈቃደኛ ስላልሆነ ፍርድ ቤቱ በውሉ መሠረት እንዲፈፀም ትእዛዝ መሰጠት ህገ መንግሥታዊ ሀላፊነት አለበት ብዬ ስለማምንና የውል ይፈፀምልኝ ጥያቄ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚቻልና በህገመንግስቱ አንቀጽ 37 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ሊታይና ሊስተናገድ የሚገባው ጥየቄ ነው ብዬ ስለማምን፣
- በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2875 ከተደነገገው መሠረታዊ መርህ አንፃር ስንመለከተው ተጠሪ የሸጠውን ቤት ስመ ንብረት የማዛወር ግዴታ እንዳለበት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2273 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገ በመሆኑና ተጠሪ የሸጠውን የቤት ባለቤትነት ለአመልካች ለማዛወር የሚያስፈልጉ ማናቸውም ተግባራት የመፈፀም ግዴታ እንዳለበት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2281 የተደነገገ

https://chilot.me

በመሆኑና ተጠሪ የቤቱን ባለቤትነት ለአመልካች የማዛወር አስፈላጊ የሆኑ ደጋፊ ማስረጃዎች የማቅረብ ግዴታ መሆኑ በፍታብሔር 2301 በግልጽ የተደነገገ በመሆኑ አብላጫው ድምጽ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2879 (1) በተደነገገው መሠረት ሻጭ(ተጠሪ) ግዴታውን ተወጥቷል በሚል ምክንያት አመልካች ክስ ለማቅረብ የሚያስችላቸው የክስ ምክንያት የለም በማለት በሰጠው ውሣኔ ባለመስማማት የልዩነት ሀሳቤን ገልጫለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ሰው ፊርማ አለበት

ፀመ

https://chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 38935

መጋቢት 3 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች፡- 1. አቶ ወልደፃድቅ ብርሃኑ ቀረቡ

2. ወ/ሮ ፈንታነሽ ኃይሉ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ስንታየሁ አያሌው ጠበቃ አቶ ሙሉጌታ ገብሩ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፣ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 03131 ሐምሌ 27 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ብይንና የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 48885 ሰኔ 10 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ሰኔ 27 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፊው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡

የክርክሩ መሠረታዊ ጉዳይ አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤት በከሣሽነት ቀርበው በሥር ተከሣሽ የሆነው ተጠሪ፣ በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 11 ቀበሌ 19 የቤት ቁጥር 671 የሆነው የመኖሪያ ቤት ሐምሌ 5 ቀን 1992 ዓ.ም ሸጠውልናል፡፡ ቤቱንና ቤቱ የሚመለከቱ ሰነዶችና ማስረጃዎችም አስረክበውናል፡፡

ሆኖም ተከሣሽ /ተጠሪ/ ከቀድሞው የቤቱ ባለንብረቶች መስከረም 21 ቀን 1986 ዓ.ም ባደረገው ግዥ ውል መሠረት ስመንብረቱን ወደራሱ በማዛወር ካርታውን ለማስረከብ የተስማማ ቢሆንም ቤቱን በሸጡለት እነ አቶ መስፍን አሰፋ ስም የወጣ ቁጥሩ 39348 የሆነ ካርታ ከተረከቡ በኋላ ካርታውን ለእኛ ለማስረከብና ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ካርታውን እንዲያስረክቡና ስመንብረቱን እንዲያዛወሩ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪም በተከሣሽነት ቀርበው ቤቱ በሸጡልኝ ስም ያለ በመሆኑ የሽያጭ ውሉ የማይረጋ ነው፡፡ ከሣሾች /አመልካቾች/ ሚያዚያ 30 ቀን 1995 ዓ.ም

ጀምሮ እድፈጽምላቸው ማስጠንቀቂያ ሰጥተውኛል፡፡ ስለሆነም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እንደውሉ ለመፈፀም ፈቃደኛ አለመሆኑን ያወቁ ስለሆነ ክሱን ያቀረቡት ማስጠንቀቂያ ከሰጡኝ ከአንድ ዓመት ከስምንት ወር በኋላ ስለሆነ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ክሣቸው በይርጋ ይታገዳል በማለት የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በአማራጭ ሌሎች መከራከሪያዎችን አቅርበዋል፡፡ የተጠሪ ሚስት ወ/ሮ ስንታየሁ ሽፈራው በበኩላቸው በጣልቃ ገብነት በክርክሩ በመግባት ያመለከቱና የበኩላቸውን ክርክር አቅርበዋል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪና በጉዳዩ ጣልቃ ለመግባት ባለመለከቱት ወ/ሮ ስንታየሁ ሽፈራው የቀረቡት ዝርዝር ክርክር ከመግባቱ በፊት የከሣሾች /አመልካቾች/ ክስ በይርጋ ይቋረጣል ወይስ አይቋረጥም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ በአመልቾችና በተጠሪ መካከል በውልና ማስረጃ ያልተመዘገበ የቤት ሽያጭ ውል የተደረገው መስከረም 21 ቀን 1992 ዓ.ም መሆኑን ገለፆና አመልካቾች ለተከሣሹ ማስጠንቀቂያ ከሰጡበት ከአንድ ዓመት ከስድስት ወር በኋላ ስለሆነ ይኸም ክሱ የቀረበው አመልካቾች ማስጠንቀቂያ ከሰጡበት ከአንድ ዓመት ከስድስት ወር በኋላ ስለሆነ ክሱ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት በይርጋ ይቋረጣል በማለት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 245/2/ መሠረት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ አጽንቷል፡፡ አመልካቾች ተጠሪ ውሉን ለመፈፀም ፈቃደኛ ነኝ ካርታና ፕላኑን አስጨርሽ አስረክባለሁ በማለት ጥር 10 ቀን 1993 ዓ.ም በጽሑፍ መተማመኛ የሰጠ ከመሆኑም በላይ ማስጠንቀቂያ ከባፍንለትም በኋላ በውሉ መሠረት ግዴታውን ለመፈፀም ፈቃደኛ መሆኑንና ፕሮሰሱን እያስጨረሰ መሆኑን እያነጋገረን ነበር፡፡ በመጨረሻ ሚስቱ ቤቱን በሌለሁበት ነው የገዛችሁት ብላ በነገረችን በሶስተኛ ቀን ክስ መሥርተናል፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሉ የሚፈፀም የጊዜ ገደብ ያለተቀመጠለት ጅምር ቤቱን ተረክበን አሰርተን ያጠናቀቅንና ሠርቪስ ቤቶችም ያሠራን መሆኑንና ተጠሪ ውሉን ለመፈፀም ፈቃደኛ መሆኑን

ሲገልፅልን የቆየ መሆኑን ከግምት ውስጥ ሣያስገቡ፣ ለፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892/3/ የተሣሣተ ትርጉም በመስጠት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ አመልካቾች በውሉ መሠረት እንዲፈፀምላቸው ማስጠንቀቂያ ከሰጡበት ከሚያዚያ 30 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ እንደማልፈጽምላቸው የሚያውቁ መሆኑን ባቀረቡት ክስ ገልፀዋል፡፡ አመልካቾች በሥር ያላነሱትን ውሉ እንደማይፈፀም የነገረችን ሚስቱ ናት በማለት ያቀረቡት ክርክር በሕጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ክሱን ያላቀረቡ በመሆናቸው ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት በጽሑፍ መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች በሰበር አቤቱታ ያቀረቡትን ክርክር በማጠናከር በጽሑፍ የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካቾችና የተጠሪ ጠበቃ የካቲት 19 ቀን 2001 ዓ.ም በቃል ክርክር አድርገዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ የክርክሩ መሠረታዊ ጉዳይና አመልካቾች እና ተጠሪ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የሥር ፍርድ ቤቶች የአመልካቾች ክስና ጥያቄ በአንድ ዓመት ይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 በመጥቀስ የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ ለተያዘው ጭብጥ እልባት ለመስጠት የማይንቀሣቀስ ንብረት የገዛ ሰው ሻጭ በውሉ መሠረት እንዲፈፀምለት ሰለሚጠይቅበት ሁኔታና ጥያቄውን ስለሚያቀርብበት የጊዜ ገደብ የተደነገጉ ድንጋጌዎችን፣ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ አመልካቾች ተጠሪ ሐምሌ 5 ቀን 1992 ዓ.ም በገባው የቤት ሽያጭ ውል መሠረት ለመፈፀም ፈቃደኛ ባለመሆኑ በፍርድ ተገድዶ እንዲፈፀምልን በማለት ያቀረቡት ክስ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1776 እና 2892 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የቀረበ ነው፡፡

አመልካች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1776 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች መሠረት ያቀረቡት የቤት ሽያጭ ውል ይፈጽምልኝ ክስ በሕግ የተደነገገው የይርጋ ሕግ የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ነው ወይስ

አይደለም የሚለውን ነጥብ ለመወሰን በመጀመሪያ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ እንደዚሁም ድንጋጌው ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2875 መሠረታዊ መርህና ስለ ሽያጭ እና ጠቅላላ ውል ከተደነገጉ ድንጋጌዎች ጋር ሊኖረው የሚገባውን ተፈፃሚነት መመርመር ያስፈልጋል፡፡

1.የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2893 ንዑስ አንቀጽ 3 "ስለሆነም ሻጭ ውሉን እንደውሉ ቃል ለመፈፀም መዘግየቱን ከተረዳበት ጊዜ አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ውሉ እንዲፈፀምለት ካልጠየቀ በቀር ገዢው ውሉ በግዴታ እንዲፈፀም የማድረግ መብቱን ያጣል" በማለት ይደነግጋል፡፡ እዚህ ላይ በአማርኛው "መዘግየቱን ከተረዳበት" በሚለው ቁልፍ በእንግሊዘኛው "ascertained" በሚለው ቃል መካከል ልዩነት ያለመሆኑን ለመገንዘብ እንችላለን፡፡ የድንጋጌው መንፈስ ገዥ በአንድ ዓመት ውስጥ ውሉ እንዲፈፀምለት ለፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ ያለበት ሻጭ በሽያጭ ውሉ መሠረት ለመፈፀም ፈቃደኛ አለመሆኑን ካረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ እንደሆነ የእንግሊዘኛውን የቃል አጠቃቀም በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

እዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ ሻጭ በሽያጭ ውሉ መሠረት ለመፈፀም እንደማይፈልግ ገዥ ያረጋገጠ መሆኑን የማያስረዳት ግዴታ ያለበት ማን ነው? የሚለው ነው፡፡ ለዚህ መሠረታዊ ነጥብ እልባት ለመስጠት ስለውል እና ተዋዋይ ወገኖች በፍትሐብሔር ሕጉ የተቀመጠ የሕግ ግምቶችን ማየት አስፈላጊ ነው፡፡

በሕግ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች ባቋቋሟቸው ሰዎች ላይ ሕግ ናቸው በማለት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1731 ንዑስ አንቀጽ 1 የደነገገ ሲሆን ውሎች በተዋዋይ ወገኖች መካከል ሊኖር የሚገባውን የቅንነት የመተማመን ግንኙነት መሠረት በማድረግ በቅን ልቦና ሊተረጎሙ እንደሚገባ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1732 ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ስናየው ተዋዋይ ወገኖች በተዋዋሉት የውል ቃል መሠት ውሉን የመፈፀም ፍላጎትና ቅን ልቦና ያላቸው መሆኑ የውል ሕግ ግምት የሚወስድበት ጉዳይ በመሆኑ ገዥ ሻጭ በሽያጭ ውሉ በገባው የውል ቃል መሠረት እንደሚፈጽም የተለያዩ የተስፋ ቃሎችን ሲሰጠው የቆየ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ የለበትም፡፡

በተቃራኒው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌን ጠቅሶ የሚከራከር ሻጭ ከገዥ ጋር ባደረገው የቤት ሽያጭ ውል መሠረት ለመፈፀም ፍላጎት የሌለው መሆኑን ገዥ በማያሻማ ሁኔታ እንዲያውቅ እና እንዲረዳው ያደረገ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ አለበት፡፡ ሻጭ በውሉ መሠረት ለመፈፀም እንደማይፈልግ

በእርግጠኝነት ገዥ እንዲያውቅ ካደረገው ከአንድ ዓመት በኋላ የሽያጭ ውሉ በፍርድ ኃይል እንዲፈፀምለት የጠየቀ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ አለበት፡፡ ስለሆነም የማይንቀሣቀስ ንብረት የሸጠ ሰው ሻጭ የሽያጭ ውሉ መሠረት የቤቱን ይዞታና የባለቤትነት ሰነዶች ለገዥ ያላስረከበ ከሆነ ውሉን ለመፈፀም ፈቃደኛ አለመሆኑንና በጽሑፍና በማያሻማ ሁኔታ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1789 ንዑስ አንቀጽ 3 በሚደነግገው አይነት ለገዥ ካሣወቀው ከአንድ ዓመት በኋላ የውል ይፈፀምልኝ ክስ ያቀረበ መሆኑን ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡

- ሻጭ በውሉ መሠረት የቤቱን ይዞታና ለገዥ አስተላልፎ ከሆነ ገዥ ሻጭ በውሉ መሠረት ይፈጽማል የሚለውን ዕምነት የሚያጠናክርና ውሉም በከፊል መፈፀም መጀመሩን የሚያሣይ መሆኑን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2875 እና ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2274 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም ሻጭ የቤቱን ባለሀብትነት ለገዥ ለማስተላለፍ እንደማይፈልግና የቤቱን ይዞታ ሻጭ በመልቀቅ እንዲያስረክበው የከፈለውንም ገንዘብ ገዥ እንዲወስድ በማያሻማ ሁኔታ የፍትብሔር ሕግ ቁጥር 1789 ንዑስ አንቀጽ 3 በሚደነግገው አይነት ለገዥ ያሣወቀ መሆኑን ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡

- ሻጭ የቤቱን ሰነዶች ለገዥ አስተላልፎ የቤቱን ይዞታ ይዞ በሚገኝበት ጊዜ የቤቱን ሰነዶች ሻጭ እንዲመልስለት የከፈለውን ገንዘብ እንዲወስድ በማያሻማ ሁኔታና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1789 ንዑስ አንቀጽ 3 በሚደነግገው አይነት ለገዥ ያሣወቀ መሆኑን ማስረዳት የሚጠበቅበት ሲሆን ከላይ ከተጠቀሱት ሁኔታዎች በአማራጭ ሻጭ ውሉ እንዲፈርስለት ወይም እንዲሰርዝለት በፍርድ ቤት ክስ አቅርቦ በውሉ መሠረት የመፈፀም ፍላጎት የሌለው መሆኑን ገዥ እንዲረዳው ከተደረገ ከአንድ ዓመት በኋላ የውል ይፈፀምልኝ ክስ ገዥ ያቀረበ መሆኑን ወይም በሕግ እውቅና ላለው የሽምግልና ተቋም ሻጭና ገዥ በነበራቸው ድርጅር ሻጭ ውሉን ለመፈፀም እንደማይፈልግ ገዢ እንዲረዳው ከተደረገ ከአንድ ዓመት በኋላ ክሱን ያቀረበው መሆኑን የማስረዳት ግዴታ አለበት፡፡ በአጠቃላይ ሻጭ በገባው የሽያጭ ውል ቃል መሠረት ለመፈፀም ፍላጎት የሌለው መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ ለገዥ ካሣወቀውና ገዥም ይህንኑ ከተረዳና ካረጋገጠ ከአንድ ዓመት በኋላ የውል ይፈፀምልኝ ክስ ገዥ ያቀረበ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ አለበት፡፡

ሻጭ በውሉ መሠረት ለመፈፀም የማይፈልግ መሆኑን ገዥ ያረጋገጠ መሆኑን ገዥ ውሉ እንዲፈፀምለት ማስጠንቀቂያ መስጠቱንና ማስጠንቀቂያ ከሰጠ በኋላ ሻጭ

በውሉ መሠረት አለመፈፀሙን በማየት ብቻ ለማረጋገጥ አይችልም፡፡ ሻጭ ገዥ ማስጠንቀቂያ ከሰጠው በኋላም ቢሆን የተለያዩ ችግሮችን እያነሣ በመካከላቸው ያለውን የመተማመንና የቅን ልቦና ግንኙነት ተጠቅሞ ከአንድ ዓመት በላይ ውሉን ሣይፈፀም የሚቆይበት አጋጣሚ ያለ ሲሆን በዚህ ጉዳይም ተጠሪ በሽያጭ ውሉ መሠረት ለመፈፀም የተለያየ ፕሮሰስ እየፈፀመ መሆኑን ለአመልካቾች በመግለጽ አመልካቾች ክስ ከማቅረብ እንደዘገዩ ያደረጋቸው መሆኑን በማንሣት አመልካቾች ተከራክረዋል፡፡ ስለዚህ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 ይርጋ ተፈፃሚነት የሚኖረው ገዥ ለሻጭ ማስጠንቀቂያ የሰጠበትን ቀን መነሻ በማድረግና ጊዜውን በማስላት ሣይሆን ሻጭ በውሉ መሠረት የመፈፀም ፍላጎት የሌለው መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ ገዥ እንዲያውቀው ያደረገበትን ቀን መነሻ በማድረግ መሆን ይገባዋል፡፡ ከዚህ አንፃር ስናየው የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካቾች በውሉ መሠረት እንዲፈፀምላቸው ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ የሰጡበትን ቀን መነሻ ጊዜውን አስልቶ የአመልካቾች ክስ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. በሁለተኛ ደረጃ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚነት የሚኖረው በሻጭና በገዥ መካከል የተደረገው ውል የማይፈፀምበት የመጨሻ ቀን በጥብቅ የተወሰነ ከሆነ በውሉ የተወሰነ ነው የጊዜ ገደብ ካለፈ ከአንድ ዓመት በኋላ ገዥ የውል ይፈፀምልኝ ክስ ማቅረቡን በማስረዳት እንደሆነ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2875 መሠረታዊ መርህና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2331 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች ጋር አጣምሮ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህም አንፃር ስናየው በአመልካቾችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ውል፤ ውሉ የሚፈፀምበትን ጭብጥ የጊዜ ገደብ የማያስቀምጥ በመሆኑ በጉዳዩ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2875፣ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 እና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2331 ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የላቸውም፡፡

3. በሶስተኛ ደረጃ የሚነሣው ጥያቄ በዚህ ጉዳይ ተጠቃሽና ተፈፃሚ መሆን ያለበት የይርጋ ሕግ ድንጋጌ የትኛው ነው? የሚለው ነው፡፡ ሻጭ በውሉ መሠረት የመፈፀም ፍላጎት የሌለው መሆኑን ለገዥ በማያሻማ ሁኔታ ያሣወቀ መሆኑን ባላስረዳበት ሁኔታ ወይም የሽያጭ ውሉ ውሉ የሚፈፀምበትን ጥብቅ የጊዜ ገደብ

ባልተገለፀበት ሁኔታ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው የአንድ ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ ተፈፃሚነት የለውም፡፡ በልዩ የሕግ ድንጋጌ የተቀመጠዉ የይርጋ ጊዜ ገደብ ተፈፃሚነት በማይኖረው ጊዜ ወይም በልዩ ሁኔታ የተደነገገ የይርጋ የጊዜ ገደብ ከሌለ ውል ይፈፀምልኝ በሚል መነሻ የሚቀርቡ ክርክሮች ላይ ተፈፃሚት ያለው የይርጋ ሕግ ድንጋጌ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 እንደሆነ ይህንን ድንጋጌዎች ይዘት በመመርመር ለመረዳት ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ከአመልካቾች ውሉን ለመፈፀም ፍላጎት የሌለው መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ ካሣወቀችው ከአንድ ዓመት በኋላ ክሱን ያቀረቡ ስለመሆኑ አላስረዳም፡፡ ስለሆነም በዚህ ጉዳይ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ 3 ተፈፃሚነት የለውም፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች ከላይ በዝርዝር ያስቀመጥናቸውን ምክንያቶችና የሕግ ድንጋጌዎች ሣያገናዝቡ የአመልካቾች ጥያቄ በአንድ ዓመት ይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. አመልካች ያቀረቡት የውል ይፈፀምልኝ ክስ በይርጋ የማይታገድ በመሆኑ አመልካችና ተጠሪ ሌሎች ተከራካሪዎች የሚያቀርቡትን ክርክር በመመርመርና በመመዘን ጉዳዩን ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 341/1/ መሠረት መልሰን ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍር ቤት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. የአመልካቾች ክስ በይርጋ አይታገድም ብለናል፡፡
4. በሥር ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መጋቢት 3 ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 39175

መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ በለጡ ጋሼ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- እነ አንዱአለም ቴድሮስ /3 ሰዎች/ ጠበቃ ዘውዱ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር የቀረበው አመልካች የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 4931 የሰጠውን የአፈፃፀም ትእዛዝ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ሰሚ ችሎት ማጽደቃቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡

የአቤቱታቸው ምክንያት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ሐምሌ 18 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው የአፈፃፀም ትእዛዝ ነው፡፡ የከፍተኛው ፍርድ የአሁን አመልካች በፍርድ የሚፈለግባቸውን ገንዘብ ከፍለው ያልቀረቡ በመሆኑ ቀደም ሲል በተሰጠው ትእዛዝ መሰረት ቤቱን ተጠሪዎች እንዲረከቡ በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይኸ ትእዛዝ መሰረታዊ ስህተት አለበት በማለት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበች ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈፃፀም ትእዛዝ አጽንቶታል፡፡

አመልካች የአፈፃፀም ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ችሎት አቅርበው የሰበር ችሎቱ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች አፈፃፀሙን የያዘው የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ ቤቱ ሁለት ግዜ በጨረታ፣እንዲወጣ ሣያደርግ ባለእዳዎች እንዲረከቡት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ይኽም መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው፡፡ የመጀመሪያው ጨረታ፣በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ህግ ቁጥር 426 መሰረት ለሰላሣ ቀናት በአየር ላይ ባለመዋሉ ፍርድ ቤቱ ሰርዞ ድጋሜ ጨረታ እንዲወጣ አዝዟል፡፡ ከዚያ በኋላ ቤቱ በህጉ መሰረት ለጨረታ ያቀረበው አንድ ጊዜ ሆኖ እያለ፣ሁለት ጊዜ ለጨረታ ወጥቶ ገዥ እንዳልተገኘ በመቁጥር የተሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት፣ ስለዚህ በሰበር ታይቶ ሊታረምልኝ ይገባል በማለት አምልክታለች፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው ቤቱ የካቲት 30 ቀን 1998 ዓ.ም ለጨረታ ቀርቦ የነበረ ሲሆን ታህሣስ 4 ቀን 1999 ዓ.ም እና ጥር 23 ቀን 1999 ዓ.ም ለሐራጅ ቀርቦ ገዥ ባለመገኘቱ ነው እኛ እንድንረከብ ፍ/ቤቱ ትእዛዝ የሰጠው፡፡ ስለሆነም በህጉ መሰረት የተሰጠ የአፈፃፀም ትእዛዝ ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለቱ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት ቤቱን ይሸጥ ካለ በኋላ ብር 8000(ስምንት ሺህ) በችሎት እንዲከፍል አድርጓል፡፡ ከዚህ በኋላ ቤቱ ይረከቡ ማለት መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርመረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪዎች ቤቱ የካቲት 30 ቀን 1998 ዓ.ም ለሐራጅ ቀርቦ ነበር በማለት ያቀረቡትን ክርክር ስንመረምረው፣ቤቱ ለሐራጅ ማስትወቂያ እንዲወጣበት ትእዛዝ ከተሰጠ በኋላ በአፈፃፀም የተሰጠው ትእዛዝ መብታችንን ይነካል የሚሉ ጣልቃ ገቦች በመቅረባቸው ጨረታው ሂደት አፈፃፀሙን

በያዘው ፍርድ ቤት የእግድ ትእዛዝ በመሰጠቱ ምክንያት የተቋረጠ መሆኑን፣የከፍተኛው ፍርድ ቤት መጋቢት 5 ቀን 1998 ዓ.ም ከሰጠው ትእዛዝ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ተጠሪዎች ቤቱ የካቲት 30 ቀን 1998 ዓ.ም የጨረታ ማስታወቂያ ወጥቶበት ለሐራጅ ቀርቧል በማለት ያቀረቡት ክርክር ተገቢነት ያለው ሆኖ አላገኘውም፡፡

ከፍተኛው ፍ/ቤት የጣልቃ ገቦቹን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የተቋረጠው የሐራጅ ሂደት እንዲቀጥልና ቤቱ ታህሣስ 10 ቀን 1999 ዓ.ም ለሐራጅ እንዲቀርብ፣የጨረታው ማስታወቂያ እንዲወጣ ጥቅምት 20 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ መሰረት የሐራጅ ማስታወቂያው ታህሣሥ 3 ቀን 1999 ዓ.ም ወጥቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም የሐራጅ ማስታወቂያው በአየር ላይ ለሰላሣ ቀናት መቆየት ያለበት ስለመሆኑ በፍታብሔር ስነ ስርአት ሕግ ቁጥር 426 የተደነገገ መሆኑን በመግለጽ ይህንን ስርአት ባሟላ መልኩ ቤቱ በሐራጅ ማስታወቂያ ወጥቶ ጥር 23 ቀን 1999 ዓ.ም ለሐራጅ ሽያጭ እንዲቀርብ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ የሐራጅ ማስታወቂያውም ጥር 3 ቀን 1999 ዓ.ም ወጥቶ ገዥ አልቀረበም ስለዚህ ቤቱን እንድንረከብ በማለት የፍርድ ባለመብት በጠየቁት መሰረት የፍርድ ባለመብት ቤቱን እንዲረከቡ በማለት ጥር 24 ቀን 1999 ዓ.ም ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የፍርድ ባለመብት የሆኑት ተጠሪዎች ቤቱን እንዲረከቡ በተደጋጋሚ ትእዛዝ ሲሰጥ ቆይቶ ሰኔ 8 ቀን 1999 ዓ.ም አመልካች በፖሊስ ተይዘው እንድትቀርቡ አድርጓል፡፡ በዚህ ቀን አመልካች ብር 8000(አምስት ሺህ ብር) የከፈለ ሲሆን ቀሪውን እዳ አጠቃልላ ከፍላ እንድትቀርብ በማለት ለሐምሌ 18 ቀን 1999 ዓ.ም ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ሐምሌ 18 ቀን 1999 ዓ.ም እዳውን አጠቃልለው ከፍለው ባለመቅረባቸው፣የከፍተኛው ፍ/ቤት የፍርድ ባለመብት ቤቱን እንዲረከቡ የሚል ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

አፈፃጸሙን የያዘው የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪዎች ቤቱን እንዲረከቡ ትእዛዝ የሰጠው በሕጉ የተቀመጠውን፣ሥርዓት በማሟላት አይደለም፡፡ ምክንያቱም የካቲት 30 ቀን 1998 ዓ.ም የተደረገውን የሐራጅ ሒደት ራሱ ፍርድ ቤቱ አግዶታል፡፡ ከዚህ በኋላ የሚከናወኑ የሐራጅ ሂደቶች እንደ አዲስ መደረግ ያለባቸው ናቸው፡፡ ጥር 10 ቀን 1999 ዓ.ም የተከናወነው፣ሐራጅ የሐራጅ ማስታወቂያው ጥር 3 ቀን 1999 ዓ.ም ወጥቶ በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 426 የተደነገገውን አስገዳጅ ስርአት ያላሟላና የሐራጅ ማስታወቂያው ሰባት ቀን ብቻ በአየር ላይ ውሎ የተፈፀመ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ይኸ ስርአት ያልተሟላ መሆኑን በማየት ሰርዞታል፡፡

ቤቱ የፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 426 መስፈርት ባሟላ ሁኔታ የሐራጅ ማስታወቂያ ወጥቶ ለሐራጅ ያቀረበው አንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ የፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 428 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት የፍርድ ባለመብቱ እንዲረከብ የሚያደርገው የሕጉን ስርአት በተከተለና ባሟላ ሁኔታ ሁለት ጊዜ የሐራጅ ማስታወቂያ ወጥቶና ቤቱ ለሐራጅ ቀርቦ ገዥ ሣይገኝ ሲቀር ብቻ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ቤቱ በትክክለኛው መንገድ ለሐራጅ የቀረበው ጥር 23 ቀን 1999 ዓ.ም ብቻ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ቤቱ በድጋሜ ለሐራጅ እንዲቀርብና የሕጉን ስርአት ባሟላ ሁኔታ የሐራጅ ማስታወቂያ እንዲወጣ ሣያደርግ ቀደም ብለው ያወጣውንና የህጉን አስገዳጅ ሁኔታ የማያሟላውን የሐራጅ ስርአት፣ እንደትክክለኛ ሐራጅ በመቁጠር ቤቱ ሁለት ጊዜ ለሐራጅ ቀርቦ ገዥ አላገኘም በማለት ተጠሪዎች ቤቱን እንዲረከቡ የሰጠው ትእዛዝ በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 428 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ የሚጥስ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ቤቱን ይረከቡ በማለት የሰጠውን ትእዛዝ በመተው አመልካች እዳቸውን በጥሬ ገንዘብ እንዲከፍሉ የፈቀደና በዚህም መሰረት አመልካች ሰኔ 8 ቀን 1999 ዓ.ም ስምንት ሺ ብር/8000/ በችሎት የከፈሉ

መሆኑን የፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ያሣያል፡፡ ከዚህ በኋላ አፈፃጸሙ በማይንቀሣቀስም ንብረት ላይ እንዲቀጥል ለማድረግ ካስፈለገ፣የአፈፃፀም ስርአቱን እንደ አዲስ በቤቱ ላይ እንዲቀጥልና የሐራጅ ማስታወቂያ ማውጣት ሲገባው የተወውና የተቋረጠውን የአፈፃፀም ስርአት በማስታወስ ቤቱን ተጠሪዎች እንዲረከቡ በማለት የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ ግደፈት ያለበት ነው፡፡ በመሆኑም የከፍተኛ ፍርድ ቤት አፈፃፀሙን ሲመራ የጣሳቸውን አስገዳጅ የስነ ሥርአት ድንግጌዎች እያሉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎትና ሰበር ችሎት ትእዛዙን ማጽናታቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወሰነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሐምሌ 18 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
3. የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች በፍርድ የተወሰነባቸውን የቀረባቸውን እዳ ለመክፈል የሚችሉ ከሆነ እንደ ክሱ እንዲያደርግ አመልካች እዳውን ለመክፈል ካልቻሉ፣ቤቱ የሕጉን ሥርአት በጠበቀ ሁኔታ በሐራጅ ተሸጦ የተጠሪዎች እዳ እንዲከፈል ያደርግ ዘንድ ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ህግ ቁጥር 343/1/ መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 39485

መጋቢት 17 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የህፃን ሰላማዊት ቴዎድሮስ ሞግዚት - ወ/ሮ ፍርቱና ገ/መድህን ቀረቡ

ተጠሪ፡- መምህር ሚካኤል ግደይ - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች በ17/07/1999 ዓ.ም በፃፉት የአፈፃፀም ክስ በ06/07/1999 ዓ.ም በተሰጠው ውሣኔ መሰረት እንዲፈጸምላቸው ይታዘዝላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው በአሁኑ ተጠሪ ላይ በማእከላይ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመሰረቱት የአፈፃፀም ክስ መነሻ ሲሆን የአሁኑ ተጠሪም በፍርድ ባለእዳነታቸው ቀርበው ፍርዱን እንዲፈጽሙና የማይፈጽሙበት ምክንያት ካለም እንዲያስረዱ ተደርገው በዋናው ጉዳይ በተሰጠው ውሣኔ መሰረት መኪናዋን ለፍርድ ባለመብት ለሆኑት ለአሁኗ አመልካች እንዲያስረክቡ ታዝዞ አረካካቢ አካልም ተመድቦና መኪናዋ ላይ ጐድለዋል የሚባሉትን እቃዎችን ከዋጋ ግምት ዝርዝር ጋር ለፍ/ቤቱ እንዲገልጽ ተደርጐ ይኸው ከተፈፀመ በኋላ የአፈፃፀም ከሣሽ የነበሩት አመልካች መኪናዋን ከእነጉድለቷ ተረክበዋል፡፡ አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤትም በመኪናዋ ላይ ጐደሎ የተባሉት እቃዎች በውሣኔ መኪናዋ ላይ እንዳሉ ተረጋግጦ መወሰኑንና የጐደለቱም መኪናዋ በአፈፃፀም ተከሣሽ እጅ መኪናዋ እንዳለች በርክክቡ ወቅት መሆኑን አረጋግጦ በርክክቡ ወቅት ጐድሎ የተገኙትን ዝርዝረ ንብረቶች በአይነታቸውና በብዛታቸው የሚጨርሱትን ዋጋ በወጋ ማቅረቢያ ፕሮፎርማ ከሦስት የተለያዩ ድርጅቶች እንዲሰባሰብ አድርጐ ጐደሉት የተባሉት የመኪና እቃዎች ብር

https://chilot.me
66,520.00(ስልሳ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ብር) መሆኑን አረጋግጦ ይህንኑ ገንዘብ አፈፃፀም ተከሣሽ ለአፈፃፀም ከሣሽ እንዲተኩላቸው በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ትእዛዝ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኛቸውን አቅርበው ይኸው ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት ጐደሉ በተባሉት የመኪና እቃዎች ላይ የሰጠው ትእዛዝ መኪናዋ በቀጥታ ክስ ጊዜ ተገምታ የቀረበችበትንና በውሣኔው ላይም መኪናውን ከሣሽ ትረከብ ተብሎ ከተወሰነው ሁኔታ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ አፈፃፀሙ የተመራው ከስነ ስርአት ውጪ መሆኑን ጠቅሶ ጐደሉ ለተባሉት የመኪናዋ እቃዎች የአሁኗ አመልካች ሊከፍላት የሚገባው የገንዘብ መጠን በዋናው ክስ ጊዜ የተጠቀሰው ብር 30,000.00(ሰላሳ ሺህ ብር) ነው በማለት የስር ፍ/ቤትን ትእዛዝ በመሻር ወስኗል፡፡ የአሁኗ አመልካች በዚህ ቅር በመሰኘት አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት ስላላገኙ በዚህ ችሎት የሰበር አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

አመልካች ሐምሌ 21 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት 2/ሁለት/ ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅረበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ በዋናው ጉዳይ በተወሰነው ውሣኔ መኪናዋን እንዲረከብ የሚል ሆኖ እያለና በርክክቡ ወቅትም የመኪናዋ እቃዎች በተጠሪ መጉደላቸው የተረጋገጠ መሆኑን አፈፃፀሙን የያዘው የስር ፍ/ቤት በገለፀበት ሁኔታ በዋናው ክስ ላይ የመኪናዋን ዋጋ ብር 30,000.00(ሰላሳ ሺህ ብር) ብለሽ ገምተሻል ተብሎ የእቃዎችን የገበያ ዋጋ ባላገናዘበ መልኩ ከስር ፍ/ቤት ትእዛዝ መሻሩ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር የካቲት 26 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተደምጧል፡፡

የጉዳዩ አመልጣጥ አጠር አጠር ባመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ትእዛዝና አግባብነት ካላቸው የሕግ

https://chilot.me
ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መረምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የመኪናዋ ርክክብ ሲፈጸም መጉደላቸው የተረጋገጡትን እቃዎችን ለመተካት የታሰበው የእቃዎች ዋጋ ውድቅ ሁኖ የእቃዎቹ ዋጋ ሊሆን የሚገባው የዋናው ጉዳይ ክስ ሲመሰረት በአመልካች የተገለፀው ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኗ አመልካች በቀጥታ ክስ ወቀት መኪናውን የገመቱት በብር 30,000.00(ሰላሳ ሺህ ብር) ሁኖ የጠየቁት ዳኝነት መኪናዋን እንዲረከቡ ይወሰንላቸው ዘንድ መሆኑን፣በቀጥታ ክስ ወቅት የተሰጠው ውሣኔም አመልካች መኪናዋን እንዲረከቡ የሚል መሆኑንና በአፈፃፀም ወቅት አመልካች መኪናዋን ሲረከቡ የጐደሉት የመኪና እቃዎች ተረጋግጠው በወቅቱ የገበያ ዋጋም የጐደሉትን እቃዎች ለመተካት ዝቅተኛው የጨረታ ዋጋም ብር 66,520.00(ስልሳ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ብር) መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ የአፈፃፀም ክስ የሚቀርበው በውሣኔው መሰረት እንዲፈጸም ስለመሆኑ ከ1958ቱ የፍትሐብሔር ሥነ ስርአት ህግ ሰባተኛ መጽሐፍ ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመመልከት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ አከራካሪውና ምላሽ የሚያስፈልገው ጉዳይ በቀጥታ ክስ ወቀት የተገመተ የንብረት ግምት በአፈፃፀም ወቀት ንብረቱ በዓይነት ካልተገኘ እና ንብረቱን በዓይነት ለመተካት የንብረቱ ዋጋ ቀድሞ ከተገመተው ግምት በልጦ ሲገኝ አፈፃፀሙ ሊሆን የሚገባው በቀድሞው ግምት ወይስ ንብረቱን በዓይነት ለመተካት በሚያስችል የወቅቱ ተገቢ ዋጋ? የሚለው ነጠብ ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ ተገቢ ምላሽ ሊገኝ የሚችለው በቀጥታ ክስ ወቀት የተሰጠውን ውሣኔ እና የገበያን የተለዋዋጭ ባህርይ ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ሲቻል ነው፡፡ እንዲሁም አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት ለአፈፃፀሙ ተስማሚ በሆነ መንገድ ፍርዱ እንዲፈጸም ትእዛዝ የመስጠት ሥልጣን ያለው መሆኑም ሊስተዋል ይገባል፡፡ በመሆኑም በቀጥታ ክስ ወቀት የነበረው የንብረት ግምት በአፈፃፀም ወቅት ንብረቱ በፍርድ ባለእዳ እጅ በነበረበት ሁኔታ ጉድለ መገኘቱ

https://chilot.me
ከተረጋገጠ በዓይነት ለፍርድ ባለመብቱ እንዲያስረክብ እስከተወሰነ ድረስ የጐለውን የንብረቱን ክፍል እንዲተካ ማድረግ በዋናው ፍርድ ከተሰጠው ውሣኔ ውጪ ሊባል የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡ የመኪና እቃዎች ዋጋ ከፍና ዝቅ የሚል መሆኑ እየታወቀም አንዴ ተገምቶ የቀረበ ዋጋ ሁል ጊዜ ተቀባይነት አለው ለማለት እይቻልም፡፡ የፍርድ ባለመብት ንብረቱን በዓይነት እንዲረከብ ከተወሰነ እና የፍርድ ባለእዳው እንደፈርዱ የማይፈጽምበት ምክንያት ያለኖሩ ሲረጋገጥ የፍርድ ባእዳው ንብረቱን በዓይነት እንዲያስረክብ፣ በዚህ ወቅትም ለአፈፃፀሙ ተስማሚ የሆነ መንገድ መከተል የፍርድ አፈፃፀም ስርአት የግድ የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ አንድ ፍርድ ለፍርድ ባለመብት እንደፍርዱ ተፈጽሞለታል ለማለት እይቻልም፡፡ በመሆኑም በትግራይ ብ/ክ/መንግስት የማእከላይ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት ለክርክሩ ምክንያት የሆነችው መኪና ጐደሉ የተባሉትን እቃዎች በተመለከተ ለአመልካች እንዲተካላቸው ፕሮፎርማ እንዲሰባሰብ በማድረግ ዝቅተኛው ዋጋ እንዲከፈል ማድረጉ የአፈፃፀም ክስ አቀራረብና የአፈፃፀም ውሣኔ አሰጣጥ ሥርአትን ባልተከተለ አኳኋን ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ይልቁንም የዚህ ፍ/ቤት አካሄድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 እና 392 ስር የተመለቱትን ድንጋጌዎችንና መኪናዋ በፍርድ ባለእዳ እጅ በነበረችበት ወቅት እቃዎቹ የመጉደላቸውን ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ነው፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሣኔ ግን አመልካች በዋናው ፍርድ መኪናዋን እንዲረከቡ የተወሰነውን ውሣኔ እና የመኪና እቃዎች የገበያ ዋጋን ተለዋዋጭነት እንዲሁም አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት ለአፈፃፀሙ ተስማሚ በሆነ መንገድ ፍርዱ እንዲፈጸም ትእዛዝ ለመስጠት ስልጣን ያለው መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 392/1/ ያስቀመጠውን መንገድ ያላገናዘበ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን ትእዛዝ ሣያርም መቅረቱ ባግባቡ ሁኖ አልተገኘም፡፡ ሲጠቃለልም መጋቢት 06 ቀን 1999 ዓ.ም በተሰጠው ዋና ውሣኔ ላይ የሰሌዳ ቁጥር ትግ 03-00778 መኪና አመልካች እንዲረከቡ ከተወሰነ በኋላ በአፈፃፀም ደግሞ

https://chilot.me

መኪናውን ሣይሆን ብር 30,000.00(ሰላሳ ሺህ ብር) ይከፈላት ተብሎ መወሰኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 እና 392 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ውሣኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በትግራይ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 23377 ግንቦት 26 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጠቶ በዚሁ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በፍ/መ/ቁ. 25095 ሰኔ 26 ቀን 2000 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የትግራይ ብ/ክ/መንግስት የማእከላይ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 08699 የካቲት 17 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
3. ለጉደሉት የመኪና እቃዎች ለተጠሪ ለአመልካች ብር 66,520.00(ስልሳ ስድስት ሺህ አምስት አቶ ሃያ ብር) ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://chilot.me

□ስበር መ/ቁዓ ር 39579

መጋቢት 15 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዐ ልቃትር መሐመት

ሐቶስ □ልዐ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ታደሰ በላይ የአልታቤ ኮሌጅ ሥራ አስኪያጅ

ተ□ሪ፡- ዳንኤል □□ሰ ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>አ ር ት</u>

ለሰበር አቤቱ□□ መነሻ □ሆነ□ □አሠሪና ሠራተኛ ክርክር የሚመለከት ነ□፡፡ □ር□ሩ የተጀመረው በአማራ ብ/ክ/መ/በደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ በአል□ቤ ኮሌ□ ላጁ □ስ □መሠረተ□ □ሥራ □ሌን ከአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌዎች ውጪ በሆነ ሁኔታ አቋርጦብኛል በማለት ነው፡፡ ኮሌ□ም ለ□ሱ በሰጠው መልስ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ተጠሪ ተቀጥሮበት የነበረው የማስተማር ሥራ መንግሥት ባወጣው መመሪያ መሠረት በመሰረዙ ነው፡፡ ሥራው ከሌለ ተጠሪን ማሰናበት የግድ ስለሚሆን ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ማለት አይቻልም በማለት ስለመከራከሩ ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ የወረዳው ፍ/ቤትም የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር ከመረመረ በኋላ መንግሥት መመሪያ ቢያወጣም ኮሌ□ ለ□ለቁታው እንዲዘጋ አልተደረገም የሚል ምክንያት በመስጠት ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው የሚል ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ክርክሩን ከሰማ በኋላ በወረዳ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ አፅንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

□ኛም አመልካች ሐምሌ 10 ቀን 2000 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱ□ በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ አግባብ ውጪ ነው

በሚል የተሰጠውን ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከስር ጀምሮ የተደረገውን የግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ የአመልካች እና የተጠሪ ግንኙነት የተመሠረተው ጥቅምት 1 ቀን 97 ዓ.ም በተደረገው የአሠሪና ሠራተኛ ውል ላይ ነው፡፡ በአመልካቹ የተወከለው ኮሌጅ የመምህራን ማሰል□ኛ ተቋም እንደሆነ በክርክሩ ተመልክቶአል፡፡ ተጠሪ የተቀጠረውም ወደ ኮሌጁ የሚገቡትን ዕጩ መምህራን ለማስተማር /ለማሰልጠን/ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ከተቀጠረበት ጸምሮ እስከ ነሐሴ ወር 99 ዓ.ም ድረስ ሲያስተምር እንደቆየ እራሱ አረጋግጦአል፡፡ በአመልካች ክርክር እንደተገለጸው የሥራ ውሉ ሊቋረጥ የቻለው መንግሥት ባወጣው መመሪያ በፅል □ማሰል□ኛ ተቋማት ወይም ኮሌጆች ሰልጥነው የሚመጡ መምህራን በመምህርነት የማይቀበል /የማይቀጥር/ መሆኑን በመግለጹ እና በዚህ ምክንያትም ኮሌጁ የመምህራን ማሰልጠን ሥራን መቀጠል ባለመቻሉ ነው፡፡ በእርግጥ መንግሥት የተባለውን መመሪያ ስለማ□ጣቱ በተከራካሪ ወገኖች ዘንድ ያላከራከረ ከመሆኑም በላይ የሥር ፍ/ቤቶችም ይህንኑ ስለማረጋገጣቸው በውሣኔዎቻቸው ላይ አመልክተዋል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ተጠሪ የተቀጠረበት የሥራ መደብ በበቂ ምክንያት ስለመሰረዙ አላከራከረም ማለት ነው፡፡

በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28/1/መ/ እንደተመለከተው ሠራተኛው የያዘው የሥራ መደብ በበቂ ምክንያት መሠረዝ የሥራ ውልን በማስጠንቀቂያ በቂ ከሆኑ ምክንያቶች አንዱ ነው፡፡ ተጠሪ ተቀጥሮበት የነበረው የመምህርነት ሥራ የተሰረዘው በቂ በሆነ ምክንያት አይደለም አልተባለም፡፡ በተለይ የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ አግባብ ውጪ ነው ለማለት ከበቃባቸው ምክንያቶች አንዱ አመልካች ለተጠሪ አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ አልሰጠም የሚል እንደሆነ ከውሣኔው ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በእርግጥም የሥራ ውሉን ለማቋረጥ በቂ ምክንያት ቢኖርም ማስጠንቀቂያ መስጠት እንደሚገባ በሕጉ ተመልክቶአል፡፡ በሌላ በኩል ግን ማስጠንቀቂያ መስጠት ያስፈለገው ሠራተኛ□ እንዲዘጋጅ ለማድረግ እንጂ በውሉ መቋረጥ ሕጋዊነት ላይ የሚኖረው ተገቢነት ታይቶ

አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ አልሰጠም በሚል ብቻ ውሉ የተቋረጠው በአዋጅ አንቀጽ 28/1/መ/ መሠረት አይደለም ሊባል አይችልም፡፡ አመልካች አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ ባለመስጠቱ ሊኖረው የሚገባው ግዴታ በአዋጁ አንቀጽ 35 በተደነገገው መሠረት የማስጠንቀቂያው ጊዜ ታስቦ ከዚሁ ጊዜ ደመወዙን ለተጠሪ መክፈል ነው፡፡ ከዚህ ባለፈ ግን የሥራ ውሉ ከሕግ ውጪ ነው የተቋረጠው ወደሚለው ትም□ሚ መትረስ ትክክል አይደለም፡፡ ከዚህ የተነሣም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአማራ ብ/ክ/መ/የደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 27030 የካቲት 15 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 19830 ሰኔ 20 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረ□ □ሥራ □ል □ተቋረ□□ በሕጉ መሠረት በመሆኑ የሥራ ውል ከሕግ ውጪ ሲቋረጥ የሚከፈሉትን ክፍያዎች ተጠሪ ሊያገኝ አይገባም ብለናል፡፡
3. አመልካች የሥራ ውሉ ከማቋረጡ በፊት ማስጠንቀቂያ ባለመስጠቱ በአዋጅ አንቀጽ 35 መሠረት የማስጠንቀቂያ ክፍያ ይክፈል ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መ□ዝ□ ጁመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://chilot.me

የፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 34540

መጋቢት 29/2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- አሰግድ ጋሻው

ደስታ ገብሩ

ብርሃኑ አመነው

ይ/ባይ፡- አቶ ህንፃ ገ/ፃዲቅ ከጠበቃ አብርሃም ሐዲስ ጋር ቀረቡ

መ/ሰጪ፡- ወ/ሮ ህይወት ስንታየሁ ጠበቃ ዘነበ አሰፋ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይግባኙ የቀረበው የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ህዳር 19/2000 ዓ.ም በኮ.ቁ 45804 በሰጠው ፍርድ ላይ ነው፡፡

ይ/ባይ በሥርም ከሳሽ ሆነው በአሁን መ/ሰጪ ላይ አቀርበውት የነበረው ክስ ከሳሽ ቁጥር 06/1 ዲኤች/1700/96 የሆነ የቡና አቀራቢነት ፈቃድ እንዳላቸው፣ ተከሳሻም ከሳሽ የሚያቀርቡትን ቡና ተቀብለው በአ.አ. ገበያ በመሸጥ የሺያጭ ገንዘቡን ለከሳሽ እንዲልኩ የካቲት 3/1997 ዓ.ም በቁ 151/97 ውክልና የሰጡ መሆኑን፤ በዚህም መሠረት ተከሳሻ ብር 4992217.95 የሚያወጣ ቡና ሸጠው በተለየዩ ጊዜያቶች ብር 4,107,672.80 ሲከፍሉ ብር 884,545.15 ያልከፈሉ ስለሆነ ከነወጪና ኪሣራ እንዲሁም ከባንክ ወለዱ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ክሱ የቀረበለት የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም በግራቀኙ የቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ በመጨረሻ በሰጠው ውሣኔ ከሳሽ ባቀረቧቸው ሰነዶች ብር 5,080,885.70 የሚያወጡ በከሳሽ ስም የተመዘገቡ ቡናዎች ለተለያዩ ቡና ላኪዎች የተሸጡ መሆኑን የሚያስረዱ መሆኑን ጠቅሶ ከቀረቡት ሠነዶች ውስጥ በሁለት ሠነዶች ድምሩ ብር 626,239.42 ቡና የተሸጠበት የተከሳሽን ስም ስለማይጠቅስ ይህ ተቀንሶ ብር

4,454,646.30 የሚያወጣ ቡና ከሳሽን ወክለው ተከሳሽ የሸጡ መሆኑን ሠነዶች እንደሚያስረዱ አረጋግጧል፡፡ ይህን መሠረት በማድረግም ከብር 4,454,646.30 ውስጥ ብር 1,702,251.74 ተጨማሪ እሴት ታክስ የማይከፈልባቸው ሆኖ በቀሪው ብር 2,752,394.60 የተጨማሪ እሴት ታክስ 15% ታስቦ 412,859.19 ተቀናሽ ሆኖ የሚከፈል ሲሆን በዚህ ሂሳብ ስሌትም ከሳሽ የሚከፈላቸው ብር 2,339,535.40 መሆኑንና በአጠቃላይ ከሳሽ ሊከፈላቸው የሚገባው ብር 4,041,787.10 ስለሆነ ከሳሽ በክሳቸው ላይ ለተከሳሻ የተከፈለውን ኮሚሽንና ወጪ ጨምሮ ብር 4,,107,672.80 የተከፈላቸው መሆኑን ስላረጋገጡ ተከሳሽ ለከሳሽ የሚከፍሉት ነገር የለም በማለት የከሳሽን ክስ ውድቅ አድርጐታል፡፡

ይግባኙም የቀረበው በዚሁ ውሣኔ ላይ ቅር በመሰኘት ነው፡፡

ይ/ባይ ታህሣስ 3/2000 ዓ.ም ፅፈው ያቀረቡት የይግባኝ ማመልከቻም ባጭሩ፡- ክሱ ተከሳሽ በተሰጣቸው ውክልና መሠረት ቡና ሸጠው ከቡና ላኪዎች ከተረከቡት የተጣራ /Net payment/ ገንዘብ ውስጥ ብር 884,545.15 ሊከፍሉ ይገባል የሚል ሲሆን ይህ ገንዘብ ከአንድ ሠነድ በተራ ቁ.4 የተገለፀው በአፃፃፍ ስህተት ከመግባት በስተቀር ሌላው በሙሉ የተጣራ ተከፋይ ነው፡፡ የባት ገንዘብ የቡና አቅራቢ ዘንድ አይደርስም፡፡ ቡና ላኪው ቡናውን ገዝቶ የባቱን ገንዘብ አስቀርቶ የተጣራ ተከፋይ ብቻ በቼክ ነው የሚከፍለው ይህም ተከሳሽ አምነው መልስ የሰጡበት ሲሆን ከአገር ውስጥ ገቢ የባት ኤክስፐርትም ቀርበው ያረጋገጡበት ነው፡፡

ሌላው በሁለት ደረሰኝ የተመለከተው ብር 626,239.42 ቡናው ተሸጦ የተቀበሉት ራሳቸው የሥር ተከሣሽ ስለመሆናቸው በፖሊስ ጣቢያ የቼክ ጉራጅ ስለመኖሩ በፅሁፍ አቅርበን ፍ/ቤቱ አልቀበለም በማለቱ ነው፡፡

ስለዚህ በተከሳሽ እጅ ከገባው ጠቅላላ ገንዘብ ላይ በተጨማሪ እሴት ታክስ ምክንያት ብር 412,889.15 እና ከሳሽ ካቀረባቸው ሁለት ሠነዶች ላይ ያለው ብር 626,239.24 በድምሩ 1,039,089.39 ተከሳሽ እንዳልተረከበች ተደርጉ የተሰጠው ውሣኔ አግባብ ስላልሆነ ተያይዞ በሚቀርበው ማስረጃ እውነታውን በማረጋገጥ የሥር ውሣኔውን በመሻር በክሱ መሠረት ከወጪና ኪሣራ ጋር እንዲወሰንልን ሲሉ አመልክተዋል፡፡

ይህ ፍ/ቤትም ይግባኙን መርምሮ በክሱ የተጠየቀው የተጣራ ተከፋይ ሆኖ ሣለ ከቡናው ሺያጭ ቫት ተቀንሶ መታሰቡና የተጨማሪ ማስረጃ ጥያቄው መታለፉ ያለአግባብ ነው የሚለውና ሌሎች ነጥቦችን ለማጣራት መ/ሰጪ እንዲቀርቡ ትዕዛዝ በመስጠት የግራ ቀኙን የይግባኝ ክርክር ሰምቷል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ይ/ባይ የተጨማሪ ማስረጃ ለማቅረብ እንዲፈቀድላቸው ያመለከቱ ሲሆን ይኸውም መ/ሰጪ ቡናውን ሸጠው በማስረጃ ሰነዶቹ ላይ የተገለፀውን ብር 626,240.25 መቀበላቸውን የቡና ማስረከቢያ ማስረጃ ሠነድ በማያያዝ ክስ የተመሠረተ ሲሆን ገንዘቡን ስለመቀበላቸውም ዐ/ሕግ በመሠረተው ክስና በፖሊስ ምርመራ መዝገብ ከፋይ ድርጅቶች የሰጡት ማስረጃ እንዳለ ጠቅሰን ማስረጃው እንዲቀርብ እንዲታዘዝልን ጠይቀን ፍ/ቤቱ ሳይቀበለን በመቅረቱ ስለሆነ ከፖሊስ ምርመራ መዝገብ ማስረጃው የተገኘ ስለሆነ የማስረጃው ፎቶ ኮፒ ፍ/ቤቱ እንዲቀበለኝ ከፋይ ባንኩም ማረጋገጫ እንዲያቀርብ እንዲታዘዝልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

በቀረበው የተጨማሪ ማስረጃ ጥያቄ ላይም መ/ሰጪ አስተያየት እንዲሰጡበት በማድረግ ማስረጃውን ፍ/ቤቱ ተቀብሎታል፡፡

የግራቀኙን የይግባኝ ክርክር ከሥር ክሱ፣ ከቀረቡት ማስረጃዎችና በዚህ ፍ/ቤት የቀረበውንም የተጨማሪ ማስረጃ ከህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

ይግባኙን ለማጣራት በተያዘው ነጥብ መሠረት፡-

1. <u>የቫት ገንዘብን በተመለከተ</u>፡- የቡና አቅራቢ የቫት ገንዘብ የመሰብሰብ ግዴታ እንደሌለበት መ/ሰጪም አምነው የተከራከረበት ሲሆን፣ የሥር ፍ/ቤቱም ከአገር ውስጥ ገቢ የቫት ኤክስፐርት አስቀርቦ በማጣራት ያረጋገጠው ነው፡፡ ይሁን እንጂ የሥር ፍ/ቤቱ በውሣኔው ላይ እንዳሰፈረው ተከሳሽ በከሳሽ ስም የሸጡት ቡና ብር 4,454,646.30 እንደሆነ ጠቅሶ ከዚህ ውስጥ ብር 1,702,251.74 ተጨማሪ እሴት ታክስ የማይከፈልባቸው እንደሆነና በቀሪው ብር 2,752,394.60 ግን 15% የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 412,859.19 ተቀናሽ ይሆናል ሲል የሰጠው ውሣኔ በምን ምክንያት እንደሆነ ግልፅ አይደለም፡፡

በሥር ፍ/ቤት በተሰጠው የባለሙያ አስተያየትም ሆነ በሌሎች ማስረጃ እንደተረጋገጠው ቡና አቀራቢው ለቡና ላኪው ቡናውን ሲሸጥ ገዥው የቫት ክፍያውን ቆርጦ በማስቀረት የተጣራ ተከፋይ ገንዘቡን ብቸ እንደሚከፍል፣ ለቡና አቅራቢው የሚሰጠውም ቫውቸር ብቻ እንደሆነ የሚያስረዳ ነው፡፡ ይህ ሆኖ ሣለ በመልስ ሰጪም በኩል ክደው ባልተከራከሩበት ነገር የሥር ፍ/ቤቱ ከፊሉን ቫት የማይከፈልበት ከፊሉን ደግሞ ቫት የሚከፈልበት ነው ሲል የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 412,859.19 ተቀናሽ እንዲደረግ የሰጠው ውሣኔ የህግና የማስረጃ ድጋፍ የሌለው ስለሆነ ሊሻር የሚገባው ነው፡፡

በሌላ በኩል ግን ይ/ባይ በሥር ክሳቸው በማስረጃ ዝርዝር ተራ ቁጥር 4 ላይ ሊከፈለኝ ይገባል ካሉት ብር 403,785.62 ውስጥ የቫት ገንዘብ ብር 52,667.69 አብሮ ተዳምሮ ስለሆነ ይኸው የቫት ገንዘብ ብር 52,667.69 (ሃምሣ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ስልሣ ሰባት ብር ከስልሳ ዘጠኝ ሣንቲም) ተቀናሽ ሊሆን እንደሚገባው

ይህ ፍ/ቤትም የሚገነዘበው ሲሆን በይ/ባይም በኩል አምነው የተቀበሉት ስለሆነ በዚህ ረገድ ሊስተካከል የሚገባው ነው፡፡

2. <u>በተጨማሪ ማስረጃነት የቀረቡትን ሁለት ሠነዶች በተመለከተ</u>፡- ከሳሽ (የአሁን ይ/ባይ) በሥር ፍ/ቤት በቀረቡት ክስና ማስረጃ ተከሳሽ (የአሁን መ/ሰጪ) በሁለት ሠነዶች ቡና የተረከቡበትን ማስረጃ በማቅረብና ከሺያጭ የተገኘውን ገንዘብም መ/ሰጪ ስለመውሰዳቸው ከፖሊስ የምርመራ መዝገብ ውስጥ ማስረጃ ይገኛል እያሉ ፍ/ቤቱ ይህንን በማለፍ ውሣኔ መስጠቱ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ተገቢ የሆኑ ማስረጃዎችን አስቀርቦ ማጣራቱና መመርመሩ ተገቢ ሊሆን በተገባው ነበር፡፡

በዚህም መሠረት ይ/ባይ ያቀረቡትን የተጨማሪ ማስረጃ ጥያቄ ይህ ፍ/ቤት ተቀብሎ ማጣራቱ ተገቢ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

የተጨማሪ ማስረጃውንም ተቀብሎ እንደመረመረው የሥር ክርክሩና ማስረጃው እንደሚያስረዳው መ/ሰጪ ቡናውን ስለመረከባቸው ብቻ የሚያስረዳ ነው፡፡ በዚህ በቀረበው የተጨማሪ ማስረጃ ደግሞ መ/ሰጪዋ ተረክበውት የነበረውን ቡና ሸጠው ገንዘቡን በቼክ ቁጥር ABH 551202 ብር 351,117.93(ሦስት መቶ ሃምሣ አንድ ሺህ አንድ መቶ አስራ ሰባት ብር ከዘጠና ሦስት) እንዲሁም በቼክ ቁጥር ABH 505085 ብር 275,122.32 (ሁለት መቶ ሰባ አምስት ሺህ አንድ መቶ ሃያ ሁለት ብር ከሰላሳ ሁለት ሣንቲም) ስለመውሰዳቸው የሚያስረዳ ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት የሺያጭ ገንዘቡን መ/ሰጪ እንደወሰዱ የሚያስረዳ ማስረጃ በፖሊስ የምርመራ መዝገብ ውስጥ እንደሚገኝ ይ/ባይ እያመለከቱ ፍ/ቤቱ ይህን በማለፉ በዚህ ፍ/ቤት ተገኝ የተባለውን ማስረጃ በማስቀረብ መ/ሰጪም የበኩላቸውን አስተያያት እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ ይሁን

እንጂ በቀረበው የተጨማሪ ላይ መ/ሰጪ ያቀረቡት መቃወሚያ ማስረጃው ሊቀርብብን አይገባም ከማለት ውጪ ማስረጃውን በማስተባበል ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡

በመሆኑም ከተጨማሪ ማስረጃውም ሆነ ከሥር ማስረጃው ጋር በማገናዘብ ማረጋገጥ የሚቻለው መ/ሰጪዋ የተረከቡትን ቡና ሸጠው በሁለት ቼኮች በጠቅላላው ብር 626,240.25 (ስድስት መቶ ሃያ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ አርባ ብር ከሃያ አምስት ሣንቲም) ስለመውሰዳቸው የሚያስረዳ ስለሆነ የሥር ፍ/ቤቱ ይህንን ገንዘብ መ/ሰጪ ስለመቀበላቸው ማስረጃ አልቀረበበትም ሲል የከሳሽን (ይ/ባይን) ክስ ውድቅ ያደረገው አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለዚህ በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሣኔም ሊታረም የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በዝርዝር እንደተመለከተውና በሥርም በማስረጃ የተረጋገጠውን መሠረት በማድረግ የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) የሚታሰብበት ነው በማለት በብር 2,752,394.60 (ሁለት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ ሁለት ሺህ ሦስት መቶ ዘጠና አራት ብር ከስልሣ ሣንቲም) ላይ 15% (አስራ አምስት በመቶ) የተጨማሪ እሴት ታክስ በማሰብ ይ/ባይ ከጠየቁት ገንዘብ ውስጥ ብር 412,859.19 (አራት መቶ አስራ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ሃምሣ ዘጠኝ ብር ከአስራ ዘጠኝ ሣንቲም) እንዲቀነስ የሥር ፍ/ቤቱ የሰጠው ውሣኔ የህግና የማስረጃ ድጋፍ ስለሌለው በዚህ ረገድ የተሰጠውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሠረት ሽረነዋል፡፡

2. መልስ ሰጪ እጃቸው ገብቷል ተብሎ ከተረጋገጠው ከጠቅላላው ገንዘብ ብር 4,992,217.95 (አራት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ዘጠና ሁለት ሺህ ሁለት መቶ አስራ ሰባት ብር ከዘጠና አምስት ሣንቲም) ውስጥ ይ/ባይ የተከፈላቸው መሆኑን ያመኑት ብር 4,107,672.80 (አራት ሚሊዮን አንድ መቶ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሰባ ሁለት ብር ከሰማንያ ሣንቲም) ተቀንሶ ቀሪው ብር 884,545.15 (ስምንት መቶ ሰማንያ አራት ሺህ አምስት መቶ አርባ አምስት ብር ከአሥራ አምስት ሣንቲም) መ/ሰጪ ለይግባኝ ባይ ሊከፍሉት የሚገባ ገንዘብ ሲሆን፣ ከዚህ ተከፋይ ገንዘብ ውስጥ ግን በሥር በማስረጃ ዝርዝሩ ተራ ቁጥር 4 ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) ገንዘብ ብር 52,667.69 (ሃምሣ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ሰባት ብር ከስልሣ ዘጠኝ ሣንቲም) አብሮ ተደምሮ የቀረበ መሆኑ ስለተረጋገጠ ይኸው ገንዘብ ተቀናሽ ሊሆን የሚገባው ነው፡፡

በመሆኑም ከብር 884,545.15 ላይ ብር 52,667.69 ተቀንሶ ቀሪውን ብር 831,977.50(ስምንት መቶ ሰላሳ አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ ሰባት ብር ከሃምሳ ሣንቲም) ክስ ከተመሠረተበት ከመጋቢት 26/2000 ዓ.ም ጀምሮ ተከፍሎ እስካለቀ ድረስ ከሚታሰብ 9% ህጋዊ ወለድ ጋር መልስ ሰጪ ለይ/ባይ እንዲከፍሉ ተወስኗል፡፡

3. ወጪና ኪሣራ ይ/ባይ ዝርዝሩን የማቅረብ መብታቸውን ጠብቀናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://chilot.me

የሰበር መ/ቁ.35689

17/07/2001

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ፀጋዬ ገ/ዓዲቅ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሮማን ዓባይ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ሰኔ 16 ቀን 1995 ዓ.ም በተባለ ውል በአዲስ አበባ ከተማ በየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16 የሚገኝ ቁጥር 060 የሆነውን ቤት ተከሣሽ ለከሣሽ በብር 550,000 /አምስት መቶ ሃምሣ ሺህ/ ሸጠውልኝ ብር 450 ሺህ የተቀበሉ ሲሆን ቤቱን በከፊልና የይዞታ የምስክር ወረቀት አስረክበውኛል ሆኖም ግን ተከሣሽ በውሉ በገቡት ግዴታ መሠረት ስም ማዛወር ሲገባቸው ይህንን ግዴታ ያልተወጡ ስለሆነ አግባብ ባለው አካል ቀርበው ስም እንዲያዛውሩና ቤቱን የሚመለከት ግብር የተከፈለበት ደረሰኞችን እንዲያስረክቡ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪም ቀርበው በሰጡት መልስ አመልካች የቤት ሽያጭ ውጭ መደረጉን ለማስረዳት ያቀረቡት ሠነድ ውል ለማዋዋል በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያልተደረገ ስለሆነ ውሉ የፀና ስለማይሆን ክሱ ሊሰረዝ ይገባዋል በማለት ተከራክረዋል፡፡

እንደዚሁም ክርክሩ ይመለከተናል ያሉ ወገኖች ጣልቃ ለመግባት ጠይቀው ተፈቅዶላቸው የበኩላቸውን ክርክር አቅርበዋል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ ከሣሽ የቤት ሽያጭ ውል መደረጉን ለማስረዳት ያቀረቡት ሰነድ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 ላይ እንደተመለከተው ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ያልተረጋገጠ ስለሆነ እንደ ረቂቅ ከሚቆጠር በስተቀር የግዴታ ምንጭ ስለማይሆን ይህንኑ ረቂቅ ሰነድ መሠረት በማድረግ የቀረበው ክስ ተገቢነት የለውም በማለት ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

ከሣሽ የአሁን አመልካች ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ለሰበር ቀርቦ መታየት እንዳለበት በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

የዚህን ችሎት ምላሽ ማግኘት ያለበት የጉዳዩ ጭብጥም በአመልካችና በተጠሪ መካከል ተደርጓል የተባለው የቤት ሽያጭ ውል በሕግ ዓይን ውጤት የሌለው ነው ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች መወሰኑ በአግባቡ ነው ወይንስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ ያቀረቡት ተጠሪ የመኖሪያ ቤት ሽጠውልኝ ባለሀብትነቱን በስሜ ለማዛወር ፈቃደኛ ያልሆኑ ስለሆነ የሚመለከተው መንግሥታዊ ተቋም በመቅረብ ስም እንዲያዛውሩና ግብር የከፈሉበትንም ደረሰኝ እንዲያስረክቡ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡

አመልካች ተጠሪ ስም ሊያዛውሩ ይገባል በማለት ዳኝነት የጠየቁትን በተመለከተ ይህ ሰበር ችሎት ቀደም ሲል በተለያዩ መዛግብት የስም ይዛወርልኝ አቤቱታ የክስ ምክንያት የለውም ሲል የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በሌላ በኩልም ተጠሪ ግብር የከፈሉበትን ደረሰኝ ሊያስረክቡኝ ይገባል በማለት አመልካች የጠየቁት ዳኝነት በተመለከተ እነዚህ ማስረጃዎች ስም በማዛወር ረገድ አስፈላጊ ስለሆኑ አቤቱታው የክስ ምክንያት እንዳለው መገንዘብ ይቻላል፡፡

ይሁንና የማይንቀሣቀስ ንብረትን የሚመለከቱ ውሎች በሕግ ፊት የሚፀኑ እንዲሆኑ በጽሁፍ መደረግ የሚገባቸው ብቻ ሣይሆን በውል አዋዋይ ወይንም በፍርድ ቤት ፊት መደረግ እንዳለባቸው ውሉ ይህን ሥርዓት ተከትሎ ያልተከናወነ ከሆነም ግዴታን ሊፈጥር እንደማይችልና እንደ ረቂቅ እንደሚቆጠር ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723/1/2/ እና 1720 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም ቀደም ሲል በመ/ቁ. 21448 በሰጠው የሕግ ትርጉም የማይንቀሣቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚደረጉ ውሎች በውል አዋዋይ ወይንም በፍርድ ቤት ፊት ካልተረጋገጡ ውጤት የላቸውም ብሏል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሰጥ የሕግ ተርጉም በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኝ የፌዴራል ወይንም የክልል ፍ/ቤት ላይ አስገዳጅነት እንደሚኖረው በአዋጅ ቁጥር 457/97 አንቀጽ 2 ላይ ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተፈረመው የቤት ሽያጭ ውል ከፍ ብሎ በተጠቀሰው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1723/1/ እና /2/ መሠረት በውል አዋዋይ ወይንም በፍርድ ቤት ፊት መረጋገጥ ሲገባው ይህ ሥርዓት ያልተከናወነ ስለሆነና ውጤቱም በሕጉ ላይ እንደተመለከተው እንደዚሁም ሰበር ችሎቱ አስቀድሞ ለድንጋጌው በሰጠው ትርጉም መሠረት ውጤት የሌለው በመሆኑ ይህንኑ መሠረት በማድረግ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች በክስ የጠየቁትን ሣይቀበሉት መቅረታቸው ተገቢነት ያለውና የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 42893 በ13/7/98 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እንደዚሁም የፌዴራል ከፍ/ቤት በመ.ቁ. 46431 በ22/2/2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በአግባቡ ስለሆነ በፍ/ብ//ሕ/ሥ/ሥ/ ቁ. 348/1/ መሠረት በአብላጫ ድምጽ አጽንተነዋል፡፡
2. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሀሣብ ልዩነት

እኔ በአምስተኛው ተራ ቁጥር የተሰየምኩት ዳኛ አብላጫው ድምጽ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 አለመሟላት ውሉን እንደረቂቅ የሚያስቆጥር ነው፣ በሻጭና በገዥ መካከል የሚፈጥረው ግዴታ የለም በማለት በደረሰበት መደምደሚያና በተከተለው የሕግ አተረጓጎም፣ ባለመስማማት በሀሣብ ተለይቻለሁ፡፡ በእኔ እምነት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ድንጋጌ አዛዥ /አመልካች/ የሕግ ድንጋጌ እንጅ አስገዳጅ አይደለም፡፡ ስለሆነም ውሉ በፍርድ ቤት መዝገብ ሹም ወይም በውል ክፍል ፊት ያልተደረገ ቢሆንም በተዋዋዮች መካከል የፀና ውል ሆኖ ያገለግላል በማለት በሰበር መዝገብ ቁጥር 34803 ጥቅምት 27 ቀን 2001 ዓ.ም በልዩነት በምክንያትነት በዝርዝር በገለጽኳቸው የሕግ አተረጓጎም መርሆችና በዝርዝር ባሰፈርኩት ነጥብ ምክንያት በዚህ መዝገብ አብላጫው ድምጽ ከሰጠው ውሣኔ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://chilot.me

የሰበር መ/ቁ. 36040

መጋቢት 17 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሙሉ ውብሸት ጠበቃ እስክንድር ዘውዴ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፀጋ ልበሎ ወኪል እዮብ ዘነበ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በሕግ መሠረት ሣይፋቱ የኖሩ ጋብቻ ፈጽመው የነበሩ ወንድና ሴት አንዱ ሲሞት ሌላው በሕይወት የቀረው ተጋቢ የነበረው የፍቺ ወይም የሚስትነት ያረጋግጥልኝ ጥያቄ ሲያቀርብ በሕግ ረገድ ያለውን ተቀባይነት ወይም ተቀባይነት የሌለው መሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ ከሟች አለቃ ዘነበ ተፈሪ ጋር በሀገር ባህል የጋብቻ ሥነ ሥርዓት መሠረት በ1954 ዓ.ም የተጋቡ መሆኑንና አብረው እያለሙ ሁለት ልጆችን የወለዱ መሆኑን በመጥቀስ የሟች ሚስትነታቸው ተረጋግጦ ውሣኔ እንዲሰጣቸው በማህበራዊ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ሲሆን የአሁኗ አመልካችም በተጠሪነታቸው ቀርበው ከሟች አለቃ ዘነበ ተፈሪ ጋር በ1958 ዓ.ም በሀገር ባህል የጋብቻ ሥነ ሥርዓት መሠረት ጋብቻ መሥርተው አብረው ሲኖሩ ቆይተው በ1986 ዓ.ም ደግሞ ቀደሞ የነበረውን የጋብቻ ግንኙነት ወደ ብሔራዊ ጋብቻ ቀይረው ሟች እስከሞቱበት ጊዜ ድረስ ሟች ጋር አብረው ሲኖሩ የነበሩ

መሆኑን፣ በዚህ የጋብቻ ጊዜም የአሁኗ ተጠሪ ከሚች ጋር ማናቸውንም ዓይነት ግንኙነት እንዳልነበራቸው በመግለጽ እና ሚችና ተጠሪ አብረው ያልኖሩ መሆኑን በመጠቀስ ተጠሪ የሚች ነኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ ሁኖ የአመልካች ሚስትነት ተረጋግጦ እንዲወሰንላቸው ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማና ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የአመልካችን ሚስትነት አረጋግጦ የተጠሪን ደግሞ ውድቅ አድርጎ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ቅሬታቸውን አቅርበው ይኸው ችሎት ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩ በነባር የቤተሰብ ሕግ ሊታይ እንደሚገባውና በሰው ምስክርነትም ሊረጋገጥ የሚችል መሆኑን በመጥቀስ ቀደም ሲል የተሰጠውን ውሣኔ በተመለከተ አመልካች ሚስት ናቸው የተባለውን ሲያፀድቅ ተጠሪን በተመለከተ ግን ተጣርቶ እንዲወሰን በመግለጽ ለስር ፍ/ቤት መልሶለታል፡፡ ጉዳዩ የተመለሰለት የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤትም በጉዳዩ ላይ ምስክሮችን ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የአሁኗ ተጠሪ የሚች ዘነበ ተፈራ ሚስት ናቸው በማለት በድምጽ ብልጫ ወስኖ በዚህ ውሣኔ የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት በየደረጃው ላሉት ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶችም ሆነ ለክልሉ ሠበር ሰሚ ችሎት ቅሬታቸውን ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም በዚሁ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች የካቲት 16 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት 2/ ሁለት/ ገጽ የሠበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ተጠሪ ከሚች ጋር በ1954 ዓ.ም የተጋቡ መሆኑ ከጋብቻ በኋላ ቤት ሠርተው አብረው እየኖሩ ሁለት ልጆችን ወልደው ከ1970 ዓ.ም በኋላ ግን ተጠሪ ከሀገር ጠፍተው ቆይተው ሚች ሲሞቱ ከ20 /ሃያ/ ዓመታት በኋላ ወደ ሀገራቸው መመለሣቸው ተረጋግጦ

እያለ ለበርካታ ዓመታት ተለያይተው እና ከሚች ጋር በእውነታ የተፋቱ መሆኑ እየታወቀ ከቤተሰብ ሕጉ መንፈስና የሠበር ችሎቱ በሠ/መ/ቁ. 20938 በተመሣሣይ ጉዳይ ከሰጠው አስገዳጅነት ካለው ትርጉም ውጪ ተጠሪ የሚች ሚስት ናቸው ተብሎ መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ስለሆነ ሊሻር ይገባዋል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው ሚያዝያ 29 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ የመልስ ማመልከቻ የአመልካች የሰበር አቤቱታ አቀራረብ የሥነ ሥርዓት ጉድለት ያለበት መሆኑና የቅሬታ ነጥቦችም ተቀባይነት የሌላቸው እንዲሁም የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ሕጋዊ መሠረት ያለው መሆኑን በመዘርዘር የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሁኖ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው ሰኔ 24 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት 4/አራት/ ገጽ የመልስ መልስ ማመልከቻ የተጠሪን መልስ በመንቀፍ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው ዓቢይ ጭብጥ ተጠሪ ከሚች አለቃ ዘነበ ተፈሪ ጋር ከተለያዩ ከሃያ ዓመት በላይ ሆኖዋቸዋል ተብሎ ተረጋግጦ እያለ የሚች ሚስት ናቸው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከመዝገቡ መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ከሚች ጋር በ1954 ዓ.ም በባህላዊ የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት ጋብቻ ፈጽመው አብረው እስከ 1970 ዓ.ም ድረስ ሲኖሩ ሁለት ልጆችን መውለዳቸውን ከ1970 ዓ.ም በኋላ ግን ተጠሪ ከአገር ጠፍተው

ቆይተው ሚች ሲሞቱ ወደ አገራቸው መመለሣቸው፣ ተጠሪ ከአገር ከጠፉ በኋላም ለአጋቢ ዳኛ ዋስ የተጠሪ ቤተሰብ ልጃችንን አምጣልን ተብለው የነበረ ስለመሆኑ በተጠሪ ምስክሮች ጭምር መረጋገጡን፣የአመልካች ከሚች ጋር በ1958 ዓ.ም በባህላዊ የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት ጋብቻ ፈጽመው ሲኖሩ ቆይተው በ1986 ዓ.ም ደግሞ ጋብቻው በብሔራዊ ሥርዓት መፈፀሙን፣ አመልካችና ሚች ከ1958 ዓ.ም ጀምሮ ሚች እስከሞቱበት ጊዜ ማለትም እስከ 1992 ዓ.ም ድረስ አብረው መኖራቸውና በዚህ ጊዜ ቆይታቸውም 10 /አሥር/ ልጆችን ወልደው አምስቱ በህይወት ሲኖሩ ቀሪዎቹ መሞታቸውን የአመልካች ምስክሮች ቃል ያረጋገጠው ጉዳይ ስለመሆኑ ነው፡፡ የበታች ፍ/ቤቶችም ተጠሪ በውጭ ከሃያ ዓመታት በላይ መኖራቸውን ያረጋገጡበት ፍሬ ጉዳይ መሆኑን ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡

በመሠረቱ ነገሩ የቤተሰብ ሕግም ሆነ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ጋብቻ በፍቺ የሚፈርስበትን መንገድ ደንግገው እናገኛልን በነገሩ የቤተሰብ ሕግ ከባልና ሚስት ወይም ከሁለቱ አንደኛው ወገን የሚያቀርበው የመፋታት ጥያቄ እንዲወሰን የሚቀርበው ለሽምግልና ዳኞች ሁኖ የመፋታት ውሣኔ የተሰጠ መሆን አለመሆኑን አስመልክቶ ክርክር ሲነሣ ብቻ ፍ/ቤት መዳኘት የሚችል ስለመሆኑ የቁጥር 727 ድንጋጌ ያሣያል፡፡ የተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ ደግሞ ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ የሚወሰነው ባልና ሚስት በስምምነት ለመፋታት ሲወስኑና ይህንኑ በፍ/ቤት አቅርበው ውሣኔያቸው ተቀባይነት ሲያገኝ ወይም ከተጋቢዎቹ አንዱ ወይም ሁለቱ ተጋቢዎች በአንድነት ጋብቻቸው በፍቺ እንዲፈርስ በፍ/ቤት ጥያቄ ሲያቀርቡ ስለመሆኑ በአንቀጽ 76 ተመልክቷል፡፡ በስራ ላይ ባሉት የክልሎች የቤተሰብ ሕግጋትም ተመሣሣይ ይዘት ያላቸው ድንጋጌናዎችን እናገኛለን፡፡

እንግዲህ በነባሩ የቤተሰብ ሕግም ሆነ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ እንዲሁም በስራ ላይ ባሉት የክልሎች ሕግጋት የፍቺ አፈፃፀም ሥርዓት ተደንግጎ የምናገኘው

ጉዳይ ቢሆንም፡፡ ፍቺ ከሽምግልና ዳኞች ወይም ከመደበኛው ፍ/ቤት ውሣኔ ውጪ በሌላ መንገድ የሚከናወንበትን ሁኔታ ግን ሕግጋቱ ያላመለከቱ ስለመሆኑ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ባልና ሚስት ለረዥም ጊዜና በዘላቂነት በተለያዩ ምክንያቶች ተለያይተው ሲኖሩ በጋብቻ መኖር ያለመኖር ላይ ሊወሰድ የሚገባውን ሕጋዊ ግምት ነባሩም ሆነ የተሻሻሉት የቤተሰብ ሕግጋት አይገልፁም፡፡ ሆኖም የፍቺና ውጤቱ ክርክር በማናቸው ወቅት ከጋብቻና ውጤቱ ጋር በማገናዘብ ሕጋዊ ትርጉም መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህም ሕጋዊ ትርጉም በክርክሩ ፍሬ ነገር ችሎቱ የሚገነዘበው አጠቃላይ ሁኔታ በተጋቢዎች መካከል ያለው እውነታ፣ ጋብቻው የሚፈርስበትን ምክንያት መፍረሱን ከማስረዳት መለየት የጎላ ጠቀሜታ ያላቸው መሆኑ ይታመናል፡፡ እንዲሁም ተጋቢዎች የጋብቻን ግላዊ ውጤት በእውን ተግባራዊ ማድረግ አለማድረጋቸው ግንዛቤ ሊያዝበት የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የተጋቢዎች መለያየት ከተከራካሪዎች እምነትም ሆነ በሌላ መንገድ ከተረጋገጠ ፍቺ በፍ/ቤት መፈፀሙን ማስረዳት የግድ ሣይል ፍቺ መኖሩን ሕጋዊ ግምት የሚወሰድበት ነው፡፡ ይህ ስለመሆኑም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ በፊት በሠ/መ/ቁ. 20938 ሕጋዊ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪና ሟች ከ1970 ዓ.ም ጀምሮ አብረው ያልኖሩ፣ ይልቁንም ተጠሪ ከ1970 ዓ.ም ጀምሮ ከሀገር ስለጠፉ ሟች ተጠሪን እንዲያመጡ በተጠሪ ቤተሰብ በአጋቢ ዳኛ በኩል ሲጠየቁ የነበረ መሆኑ መረጋገጡ ተጠሪና ሟች የጋብቻን ግላዊ ውጤት በእውን ተግባራዊ ሣያደርጉ ምንም ግንኙነት ሣይኖራቸው ተለያይተው ሲኖሩ የነበሩ መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡ አመልካች ግን ሟች እስከሞቱበት ጊዜ ድረስ ከሟች ጋር አብረው የኖሩ መሆኑ መረጋገጡ የጋብቻን ግላዊ ውጤት በእውን ተግባራዊ አድርገው መገኘታቸውን የሚያስገነዝበን ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ከሟች ጋር ከሃያ ዓመታት በላይ ተለያይተው መኖራቸው

መረጋገጡ በ1954 ዓ.ም የተደረገው ጋብቻ በእውነታ መፍረሱን የሚያሣይ ሕጋዊ ግምት ነው፡፡ ሲጠቃለልም የበታች ፍ/ቤቶች ተጠሪ በውጭ ሀገር ከሃያ ዓመታት ቆይተው ሚች ሲሞቱ ወደ አገራቸው የተመለሡ መሆናቸውና በእነዚህ ጊዜያትም ተጠሪና ሚች ከባልና ሚስት የሚጠበቀው ግንኙነት ያልነበራቸው መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ተጠሪ በውጭ ላይ ይኖሩ የነበሩ መሆናቸው ፍሬ ነገር ከሚች ጋር ጋብቻ አልነበራቸውም ሊያስብል አይችልም በማለት መወሰናቸው የሕጉን ዓላማና መንፈስ እንዲሁም ማህበራዊ እውነታን ባለገናዘበ መልኩ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መክንያት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1/ የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 21233 ህዳር 25 ቀን 2000 ዓ.ም የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በማጽናት የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት በድምጽ ብልጫ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

2/ ወ/ሮ ፀጋ ልበሎ የሚች አለቃ ዘነበ ተፈሪ ሚስት አይደሉም ብለናል፡፡

3/ ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

4/ በ06/06/2001 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሦት ዳኞች ፊርማ አለበት

የልዩነት ሃሣብ

ስማችን በተራ ቁጥር 2 እና 5 ላይ የተጠቀሰው ዳኞች በዚህ ጉዳይ በአብላጫ ድብጽ ከተሰጠው ውሣኔ በሚከተለው አኳኋን በሃሣብ ተለይተናል፡፡

በአብላጫ ድምስ በተሰጠው ውሣኔ በሚች አለቃ ዘነበ ተፈሪና በተጠሪ ወ/ሮ ፀጋ ልበሎ መካከል የነበረው ጋብቻ ፈርሷል የተባለው ከ1970 ዓ.ም ጀምሮ ተጠሪ

ጠፍተው በመሄዳቸው ምክንያት ሟች አቶ ዘነበ ተፈሪ እስከሞቱበት ጊዜ ድረስ ከ20 ዓመት በላይ ተለያይተው ስለኖሩ የጋብቻን ግላዊ ውጤት በእውን ተግባራዊ ያላደረጉ ስለሆነ በ1954 ዓ.ም በመካከላቸው የተደረገው ጋብቻ በእውነታ ደረጃ ስለመፍረሱ ሕጋዊ ግምት ይወሰድበታል ከሚል መነሻ ሃሣብ /premise/ እንደሆነ ከውሣኔው መገንዘብ ይቻላል፡፡

ይሁንና ጋብቻ ፈርሷል ለማለት የሚቻለው በአብላጫውም ውሣኔ ላይ እንደተመለተው በነበሩ የቤተሰብ ሕግ በሽምግልና ዳኞች በሚሰጥ ውሣኔ በተሻሻለው የፌዴራልና የክልል ቤተሰብ ሕግ መሠረት ደግሞ በፍርድ ቤት በሚሰጥ ውሣኔ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሟችና በተጠሪ መካከል በዚህ መልኩ የተሰጠ የፍቺ ውሣኔ የለም፡፡ ሟችና ተጠሪ ከ1970 ዓ.ም ጀምሮ ከ20 ዓመት በላይ ተለያይተው ስለመኖራቸው በእርግጥ ተረጋግጧል፡፡ ለዚህን ያህል ጊዜ ተለያይተው መኖራቸው በእራሱ የፍቺ ውጤትን የሚያስከትል አይደለም፡፡ ይህ ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 20938 በሰጠው ውሣኔ ጋብቻው በእውነታ ደረጃ ፈርሷል ወደሚል መደምደሚያ ለመድረስ የቻለው የተጋቢዎችን ተለያይተው መኖርን ብቻ መሠረት በማድረግ ሣይሆን ተጋቢዎቹ በ1985 ዓ.ም ተጣልተው ሚስት ከቤት ወጥተው ተለያይተው ይኖሩ እንደነበር ከዚህ በኋላም ባል ሌላ ሚስት እንዳገቡና እነዚህን ሁኔታዎች በድምሩ በመመልከት የቀድሞው ጋብቻ በእውነታ ደረጃ ፈርሷል በማለት ውሣኔ የሰጠ ስለሆነ በዚህ አስቀድሞ በሰበር ችሎት በተሰጠ ውሣኔ ጋብቻው ፈርሷል የተባለው ከፍ ብሎ የተጠቀሱት የተለያዩ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ ሟችና ተጠሪ ሲለያዩ በፀብ እንዳልነበረ የተረጋገጠ ከመሆኑ በላይ ከተለያዩም በኋላ ሟችም ሆነ ተጠሪ ሌላ ጋብቻ ያልመሠረቱ ስለሆነ ተለያይተው ለረጅም ጊዜ መኖራቸው ጋብቻውን ለማፍረስ ሃሣብ እንደነበራቸው የማያመለክትና ሰበር ችሎቱ

ከላይ በተጠቀሰው የመ.ቁ.20938 ላይ ከወሰደው አቋም ጋር ተመሣሣይ ባለመሆኑ በዚህ መዝገብ የአስገዳጅነት ባህሪይ ሊኖረው ስለማይችል የአብላጫው ድምጽ ይህንኑ የሰበር ውሣኔ መሠረት በማድረግ እስከ ትግራይ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ድረስ የተሰጠውን ውሣኔ መሻሩ ተገቢነት በሌለው ሁኔታ ስለሆነ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላልተፈፀመበት ሊፀና ይገባል በማለት ከሥራ ባልደረቦቻችን በሃሣብ ተለይተናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://chilot.me

የሰበር መ/ቁ. 36460

መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡-መሐመድ ሰዓዳይ ረጃ - ጠበቃ አበራ ጣሰው ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡- 1/ አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ ፈረጅ - ቀርበዋል

2/ የህፃን ፊልሚያጀላኒ ሞግዚት ሻ/ሸዋነሽ አሰጋኸኝ - አልቀረቡም

3/ አቶ ሙክታር መሐመድ ፈረጅ - አልቀረቡም

4/ የአቶ ማሕሙድ መሐመድ ፈረጅ ወራሾች - አልቀረቡም

5/ ወ/ሮ ጀሚላ ጁሃር መሐመድ - አልቀረቡም

6/ ወ/ሮ ዘምዘም መሐመድ ፈረጅ - ..

7/ ወ/ሮ አለማ መሐመድ ፈረጅ - ..

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ክርክር ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 09 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታቸው የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ. 22079፣ ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ይሻርልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በመቀሌ ከተማ፣ የደቡብ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚሁ ፍ/ቤት በተካሄደው ክርክር የአሁኑ ተጠሪዎች ከሣሾች የአሁኑ አመልካች ደግሞ ተከሣሽ የነበሩ ሲሆን ስር ከሣሾቹ ጥቅምት 28 ቀን 1999 ዓ.ም የተፃፈ ክስ ያቀረቡ ሲሆን አጭር ይዘቱም ሰኔ 15 ቀን 1998 ዓ.ም የተደረገው ውል ሕጋዊ ስላልሆነ እንዲፈርስና በተከሣሾቹ እጅ በዚሁ ምክንያት የገቡትን ቤቶች ይመለሱልን የሚል ነው፡፡

ተከሣሹም ባቀረቡት ተቃውሞ እርሣቸውም ሆነ ከሣሾቹ በኢትዮጵያ በተለያዩ ክልሎች እንዲሁም በውጭ አገር የምንኖር ስለሆነ በአዋጅ 25/88 ዓንቀፅ 5/2/ መሠረት ክርክሩን የመዳኘት ስልጣን ያለው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንጂ የከተማው ወረዳ ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም ብለዋል፡፡

ከሣሾችም በጠበቃቸው በኩል ከላይ ለሰፈረው ተቃውሞ ታህሣሥ 23 ቀን 1999 ዓ.ም የተፃፈ መልስ የሰጡበት ሲሆን ይዘቱም ምንም እንኳ ከሣሾች በተለያዩ ክልሎች የሚኖሩ ቢሆንም ውሉ የተፈፀመው እና አከራካሪው የማይንቀሣቀስ ንብረት የሚገኘው በመቀሌ ከተማ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው፤ አዋጅ ቁ. 25/1988 ዓንቀፅ 5/2/ በውል ላይ በተመሠረተ ክርክር አይደለም፤ ተቃውሞው ውድቅ ሊሆን ይገባል የሚል ነው፡፡

የሥር ወረዳ ፍርድ ቤቱም የቀረበው ተቃውሞና መልስ ከላይ ከተመለከተው የአዋጁ ይዘት በማገናዘብ ጉዳዩ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን ስለሆነ ክርክሩን የማካሄድ ስልጣን የለኝም በማለት ጥር 14 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት ብይን ሰጥቷል፡፡

ስር ከሣሾቹ ከላይ በሰፈረው ብይን ቅሬታ በማሣደር ወደ መቀሌ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ክርክር ከተካሄደ በኋላ ፍ/ቤቱ ሚያዚያ 05 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ብይን ክርክር የተነሣበት ቤት በመቀሌ ከተማ የሚገኝ በመሆኑ እንዲሁም ውሉ የተፈፀመው በዚሁ ከተማ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 24/1/ እና

25/1/ሀ/ መሠረት ስልጣን አለው በማለት የስር ፍ/ቤት ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ሽሮታል፡፡

ጉዳዩ በስር ተከሣሹ ይግባኝ አቅራቢነት በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የታየ ሲሆን ይህ ፍ/ቤትም በፍ/ይ/መ/ቁ. 20127፣ ጥቅምት 15 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ የወረዳ ፍ/ቤቱ ስልጣን የለኝም የሚል ብይን ከሰጠ በኋላ ስር ከሣሾቹ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 245/3/ መሠረት ክሣቸውን አሻሽለው ወደ ወሰነው ፍ/ቤት ወይም ወደሌላ ፍ/ቤት ማቅረብ የሚፈቅድ ሆኖ እያለ ከፍተኛ ፍ/ቤቱ የወረዳውን ብይን መሻሩ ተገቢነት የለውም በማለት የወረዳ ፍ/ቤቱ የሰጠውን ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ሽሮታል፡፡

በዚህ የጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሣኔ ቅሬታ በማሣደርም ስር ከሣሾቹ ጉዳዩን ወደ ትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ያቀረቡት ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ወገኖች ካከራከረ በኋላ በመ.ቁ. 22079፣ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤቱ የከፍተኛ ፍ/ቤቱን ብይን ለመሻር የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 245/3/ አጣቅሶ ከሣሾቹ ክሣቸውን አስተካክለው ለሚመለከተው ፍ/ቤት ያቀርባሉ እንጂ ይግባኝ ማለት አልነበረባቸውም ማለቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንደሆነና ስር ከሣሾቹ ይግባኝ ከማቅረብ በሕግ አይከለከሉም በማለት የጠቅላይ ፍ/ቤቱን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ በመሻር የከፍተኛ ፍ/ቤቱን ብይን አጽንቷል፡፡

የአሁኑ አመልካችም ከላይ የሰፈረውን የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ይታረምልን በማለት መጋቢት 09 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ አቅርበዋል፤ መሠረታዊ ይዘቱም የቀረበው ክስና ተቃውሞ በአዋጅ ቁ. 25/1988፣ ዓንቀጽ 5/2/ መሠረት በፌዴራል ፍ/ቤቶች የሚታይ እንጂ በክልል ፍ/ቤት አይደለም፤ የትግራይ ክልል ጠቅላይ

ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 245 አተረጓጎም ረገድ የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይግባኝ ችሎት ስህተት ፈጽሟል ብሎ ማረም ቢችልም ለመሠረታዊ የክርክራችን ነጥብ የሰጠው መልስ የለም፤ ስለሆነም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል የሚል ነው።

ተጠሪዎችም ሐምሌ 29 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፤ ይዘቱ ሲታይም እየተከራከሩበት ከመጡት ክርክር ያልተለየ በመሆኑ ደግሞ መዘርዘር ሣያስፈልግ ታልፏል።

ይህ ፍርድ ቤትም የግራና ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጥ ከላይ እየተዘረዘረ በመጣው መልኩ በመገንዘብ ፣

በክሱ የተመለከተውን ጭብጥ የመዳኘት ስልጣን ያለው የትኛው ፍርድ ቤት ነው? የክልሉ ፍርድ ቤት ወይስ የፌዴራል ፍ/ቤት?

የሚለውን መሠረታዊ ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል።

ከክርክሩ መረዳት እንደተቻለው ተከራካሪ ወገኖች በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በተለያዩ ክልሎች እንዲሁም ከኢትዮጵያ ውጭ እንደሚኖሩ ነው፤ ግራ ቀኙ ወገኖችም በዚህ ነጥብ የሚካካዱ አይደሉም። አመልካቹ እያቀረቡት ያለው ክርክር ነዋሪነታቸው በተለያዩ የኢትዮጵያ ክልሎች በሆኑ ሰዎች መካከል የሚደረግ ክርክር በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1988 ዓንቀጽ 5/2/ መሠረት ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ናቸው የሚል ሲሆን ተጠሪዎቹ ደግሞ አከራካሪው ጉዳይ በመቀሌ ከተማ ውስጥ በሚገኝ ቤት የሚካሄዱ ስለሆነና ውሉም የተፈፀመው በዚሁ ከተማ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 24/1/ እና 25/1/ሀ/ መሠረት ክርክሩን የመዳኘት ስልጣን ያለው አራካሪው ቤት ባለበት የተቋቋመው የመቀሌ ደቡብ ወረዳ ፍርድ ቤት እንጂ የፌዴራል ፍርድ ቤት አይደለም ባይ ናቸው። አዋጅ ቁጥር 25/1988 የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን በማቋቋም ብቻ ሚናው የታጠረ አይመስልም፤ከዚህም አልፎ

በፌዴራል ፍርድ ቤቶችና በክልሉ ፍርድ ቤቶች መካከል ስልጣን የሚደለድል መሠረታዊ ሕግ ነው፡፡ በዚህ አዋጅ ዓንቀጽ 5/2/ መሠረት ነዋሪነታቸው በተለያዩ የክልል መስተዳድሮች በሆኑ ሰዎች መካከል የሚካሄድ ክርክር የሚስተናገድው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ነው በማለት በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ ይህ መሠረታዊ ይዘት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ውስጥ በዓንቀጽ 24/1/ እና 25/1/ሀ/ እንደተመለከተው አከራካሪው የማይንቀሣቀስ ንብረት በአንድ ክልል ስለተገኘ ብቻ ወይም ውሉ የተፈፀመው በአንድ ክልል በመሆኑ ብቻ ጉዳዩ የክልል ፍርድ ቤቶች ተፈጥሯዊ ስልጣን እንዲኖራቸው የሚያደርጋቸው አይደለም፤ ስለሆነም በመጀመሪያ ከስረ -ነገር ስልጣን አኳያ አከራካሪው ጉዳይ ሲታይ የፌዴራል ፍርድ ቤት ስልጣን መሆኑ አጠያያቂ አይደለም፤ ፌዴራል ፍርድ ቤቶችም ስልጣናቸው በሆኑ ጉዳዮች በእያንዳንዱ ክልል በቀጥታ መዋቅራቸው ዘርግተው ወይም ደግሞ ለሚመለከተው የክልል ፍ/ቤት ውክልና በመስጠት ዳኝነት እንደሚሰጡ ነው፡፡ ስለሆነም የመቀሌ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሁም የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አከራካሪው ቤት በመቀሌ ከተማ በደቡብ ወረዳ በመገኘቱ ብቻ ወይም ውሉ በዚሁ አካባቢ በመደረጉ ወይም የሚፈፀም መሆኑን ብቻ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በአዋጅ ቁጥር 25/88 ዓንቀጽ 5/2/ የተመለከተውን ድንጋጌ ተፈፃሚ እንዳይሆን ስለሚያደርግ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆነው ተገኝተዋል፤ ስለሆነም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 04156፣ ሚያዝያ 05 ቀን 1999 የሰጠው ብይን እንዲሁም የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 22079 ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፤ ይፃፍ፡፡

2. በመቀሌ ከተማ፣ የደቡብ ወረዳ ፍ/ቤት ጥር 14 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፤ ይፃፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ ወገኖች እየተከራከሩበት ያለው ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5/2/ መሠረት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ነው፤ ስለሆነም ተጠሪዎቹ ክሣቸውን ከፌዴራል ፍርድ ቤት ውክልና በተሰጠው የሚመለከተው የክልሉ ፍ/ቤት አቅርበው ይከራከሩ ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወገኖች በዚህ ፍርድ ቤት ላካሄዱት ክርክር ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፤ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://chilot.me

□ሰ/መ/ቁዓር 36756

መጋቢት 17 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

□□ሰ ጁር□

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

□ሊ መሐመት

አመልካች፡- አቶ ፀጋዬ ምትኩ ጠበቃ መኮንን አምቦ ቀርበዋል፡፡

ተጠሪዎች፡- 1/ ወ/ሮ አበበች ምትኩ ጠበቃ አረጋ ይ□ሱ ቀርበዋል፡፡

2/ አቶ ፈለቀ አላጋው ጠበቃ አረጋ ይታገሱ ቀርበዋል፡፡

ጉዳዩ ከተመረመረ በኋላ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>አ ር ት</u>

ጉዳዩ ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 24 ቀን 2000 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታቸው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካ ምድብ ችሎት በመ/ቁ. 18885 ህዳር 22 ቀን 1998 ዓ.ም እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 44695 ታህሣሥ 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጡት ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚሁ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች ከሣሽ፣ የአሁኑ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሣሾች በመሆን የተከራከሩ ሲሆን፣ ስር ከሣሹ ሰኔ 29 ቀን 1996 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የተሻሻለ ክስ አጭር ይዘቱ ተከሣሾች በየካ ክፍለ ከተማ በቀበሌ 16 ክልል ውስጥ የሚገኘውን ቁጥሩ 740 የሆነውን ቤታቸውን የካቲት 02 ቀን 1980 ዓ.ም በተጻፈ የሽያጭ ውል በብር 2ሺ000 (ሃያ ሺህ ብር) ሸጠውልኝ ቤቱንና ከቤቱ ጋር የተያያዙ አስፈላጊ ሰነዶች በወቅቱ አስረክበውኝ በቁጥጥሬ ስር ጁቶኖሉ፡፡ ይሁን እንጂ ቤቱ ገና ካር□ ያልወጣለት ስለነበር ካር□ በወቅቱ ሊያስረክቡኝ አልቻሉም ነበር፡፡ አሁን ግን ካርታው አውጥተው እንዲያስረክቡኝ

ወይም ደግሞ ፍርድ ቤቱ የገዛሁትን ቤት በስሜ እንዲዛወርልኝ (በሻሸ ስም እንዲመዘገብ) የሚያደርግ ውሣኔ ይሰጠኝ የሚል ነው።

ተከሣሾችም ጥቅምት 18 ቀን 1997 ዓ.ም በተጻፈ መልሳቸው ከሣሽ ያቀረቡት የውል ይፈጸምልኝ ጥያቄ ውሉ ተፈጸመ ካሉበት ጊዜ ወዲህ ሲታሰብ ከ16 ዓመታት በላይ ያስቆጠረ በመሆኑ ክሳቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1845 መሠረት በይርጋ የሚ□ቱት ነ□። የሽያጭ ውሉም ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ወይም በፍርድ ቤት ፊት የተፈጸመ ባለመሆኑ። እንዲሁም እኛ መሐይማን በመሆናችን ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1728/3/ መሠረት ውድቅ ነው ሊባልልን ይገባል ብለዋል።

□ሥር አ/ቤቱም □ፅራ ቀኙ ወገኖች ክርክር ከላይ በሰፈረው መልኩ ከተገነዘበ በኋላ ህዳር 22 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ብይን ወደ ሌሎች መከራከሪያ ነጥቦች ሳይገባ የቀረበው ክስ ውሉ ተደረገ ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ ክሱ እስከቀረበው ጊዜ ያለው ሲሰላ ከ10 አመት በላይ በመሆኑ ቱ□□ በአ/ብ/ሕ/ቁዓር 1845 መሠረት በይርጋ የሚ□ቱት ነው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 245/2/ መሠረት ዘግቶ□ል።

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ወገኖች ካከራከረ በኋላ በመ/ቁ/ 44695 ታህሣሥ 25 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ የስር ፍ/ቤት ውሣኔን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት አፅንቶ□ል።

ከላይ የሰፈረው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት። ቤቱ ውሉ ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ በእጁ እያለ ክሱ በይርጋ ይታገዳል ሊባል አይገባም። ተጠሪዎቹ የቤቱ ካርታ ያወጡት በ1996 ዓ.ም መጨረሻ በመሆኑና እስከዚያ ድረስ ግን ከተጠሪዎች አቅም ውጭ በሆነ ሁኔታ መንግሥት ካርታ እንዳይዘጋጅለት አግዶት የነበር ስለሆነ አመልካች ተጠሪዎቹ ካርታ ያስረክቡኝ ብዬ ክስ ልመሰርት አልችልም ነበር። ስለ□ህ ጁር□□ □ሚታሰበው ከ1996 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ መሆን ሲገባው የቤቱ ሽያጭ ውል ከተፈራረምንበት ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ መሰላቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው። ይርጋው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1846 መሠረት መሰላት ያለበት ግዴታውን ለመጠየቅ

ተገቢ ከሆነው ጊዜ ከ1996 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ ነው በማለት መጋቢት 24 ቀን 2000 □ም በተ□ፉ አቤቱታቸው ገልጸዋል።

መጋቢት 10 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎትም በግራ ቀኙ ወገኖች መካከል የቃል ክርክር የተካሄደ ሲሆን አመልካች በአቤቱታቸው ከገለጹት ሃሣብ ውጭ የሆነ ክርክር አላቀረቡም። ተከሣሾቹ በሰጡት መልስ ደግሞ ቤቱን አልሸጥንም ተያያዥ ሰነዶችም አላስረከብንም አለኝ በማለት ያቀረቡት ውል በሐሰት የተዘጋጀ ነው። ክሱ የቀረበው ከ16 ዓመታት በኋላ የካቲት 30 ቀን 1996 ዓ.ም በመሆኑና ሰኔ 29 ቀን 1996 ዓ.ም የተሻሻለ ክስ በመቅረቡ ውሉ ተደረገ ከተባለበት ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ ሲ□ሰብ በጽር□ ጽታገዳል። አመልካች የቤቱ ካርታ በ1996 ዓ.ም መጨረሻ ነው የተዘጋጀው ማለታቸው የይርጋ መቆጠሪያውን ጊዜ ወደኋላ ሊመልስ የሚችል ምክንያት አይደለም። አመልካች የ1ኛ ተጠሪ ወንድም በመሆናቸውና የቤት ችግር የነበረባቸው በመሆኑ በጥገኝነት እንዲኖሩበት የሰጠናቸው እንጂ አልሸጥንላቸውም። ውሉ የመንደር ውል በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1723 መሠረት የማይፀናና ረቂቅ ነው ብለዋል።

አርት ቤቱም □ፅራ ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጥ ከላይ ባሰፈረው መልኩ በመገንዘብ ክርክሩ በጽር□ ሊታገድ ይገባዋል ወይስ አይገባውም ? □ሚል መሠረ□ዊ ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል።

ከክርክሩ መረዳት እንደተቻለው አመልካች ባቀረቡት ክርክር የቤቱ ሽያጭ ውል የተደረገው የካቲት 2 ቀን 1980 ዓ.ም ሆኖ ቤቱንና ከቤቱ ካር□ □·□ ጸሉ □ቤቱ ሰነዶች ወዲያው ተረክበው እስካሁን ድረስ እየኖሩበት እንደሆነና ተጠሪዎችም ካርታ በወቅቱ ያልሰጧቸው በሚመለከተው አካል ካርታ እንዳይሰራለት ታግዶ ስለነበር እና በ1996 ዓ.ም መጨረሻ ግን ካርታ ተዘጋጅቶ ለተጠሪዎች እንደተሰጣቸ□ ወዲያውኑ ይህ □ስ እንደመሰረቱባቸው እኛም በጽር□□· ቂ□ መታሰብ ያለበት ከ1996 ዓ.ም መጨረሻ ጸምሮ እንጂ ውሉ ከተደረገበት ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ አይደለም የሚል ሲሆን ተጠሪዎቹ ባቀረቡት ክርክር ደግሞ የቤቱ ካርታ በ1996 ዓ.ም መጨረሻ ተሰጣቸው የሚለውን የአመልካች መከራከሪያ ነጥብ ሳይክዱ የይርጋ ጊዜው መሰላት ያለበት ውሉ ተደረገ

ከተባለበት ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 01845 መሠረት በ10 ዓመት ጹር□ ጹታገዳል የሚል የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ተገቢ እንደሆነ የሚገልጽ ነው። የሥር ፍ/ቤቶችም በሌሎች መከራከሪያ ነጥቦች ውሣኔ ሳይሰጡ ውሉ ተደረገ ከተባለበት ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች ክስ እስካቀረቡበት ጊዜ ድረስ ያለው ጊዜ ሲሰላ ከ10 ዓመታት በላይ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1845 መሠረት በይር□ ጹ□ቶ□ል በሚል ለቶ□ዩ መቋ□ ያደረጉ መሆኑ መዝገቡ ያሳያል። ይሁን እንጂ ቤቱ ካር□ □ን□ጹ□ጋጅለት በሚመለከተው አካል ታግዶ እስከ 1996 ዓ.ም መቆየቱ እና በ1996 ዓ.ም መጨረሻ ግን ካርታ ተዘጋጅቶ ለተጠሪዎቹ እንደተሰጣቸው ግራ ቀኙ ወገኖች የሚተማመኑበት ነጥብ ነው። ይህ በሆነበት ሁኔታ ደግሞ አመልካቹ ተጠሪዎቹን የቤቱን ካርታ ስጡኝ ወይም በስሜ አዘጋጁልኝ ብለው ሊከሱ የሚችሉበት የበሰለ መብት ያለመኖሩ ጸሳጸል። □አ/ብ/ሕ/ቁዓር 1846 እንደደነገገውም የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ግዴታውን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነ ጊዜ ጀምሮ ነው ይላል። አመልካቹ ለተጠሪዎቹ የቤቱን ካር□ በሚመለከተው አካል ከመሰጠቱ ከ1996 ዓ.ም በፊት ቢከሱ ኖሮ ሊፈጸም የማይችል መብት ይሆን እንደነበር ከክርክሩ መረዳት ይቻላል። በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶቹ በዚህ ጉዳይ ይርጋው መቆጠር ያለበት ውሉ ከተደረገበት ከየካቲት 02/1980 ዓ.ም ጀምሮ መሆን አለበት የሚል ትርጉም በመያዝ ክርክሩ በአ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁዓር 1845 መሠረት በ10 ዓመት ይርጋ የታገደ ነው በማለት የሰጡት ፍርድ መሠረ□ዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል።

ው ሣ ኔ

1/ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካ ምድብ ችሎት በመ/ቁ/ 18885 ህዳር 22 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 44695 ታህሣሥ 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጡት ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348 /1/ መሠረት ተሽረዋል። ይጻፍ።

2/ በዚህ ክርክር ይርጋው መቆጠር የሚጀምረው የቤቱ ሽያጭ ውል ከተደረገበት ከየካቲት 02/1980 ዓ.ም ሳይሆን የሚመለከተው አካል የቤቱን ካርታ በተጠሪዎቹ

ስም አዘጋጅቶ ከሰጠበት ከ1996 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ በመሆኑና አመልካችም በተጠሪዎቹ ላይ ክስ የመሰረቱት የካቲት 30 ቀን 1996 ዓ.ም በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁዓር 1845 መሠረት የይርጋው ጊዜ ያለፈበት አይደለም ብለናል፡፡

3/ ከይርጋ ክርክር ውጭ ባሉ ሌሎች መከራከሪያ ነጥቦች ጉዳዩን መርምሮ የመሰለውን ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341 መሠረት ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካ ምድብ ችሎት ተመልሶለ□ል፡፡ ጽ□ኣ፡፡

4/ ፅራ ቀኙ ወገኖች በዚህ ፍርድ ቤት ላካሄዱት ክርክር ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

5/ ጉዳዩ ያለቀ በመሆኑ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ኝርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://chilot.me

የሰበር መ/ቁ. 37503

24/7/2001

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- አቶ ወልደዮሐንስ ሀብትየስ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ያምሮት ሽዋረጋ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን የአሁን አመልካች አቶ ተክሉ በቀለ በተባሉ ግለሰብ ላይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ የሚች ወ/ሮ እልፍነሽ በቀለ የሕግ ባል ነኝ፡፡ ሚች ባለቤቱ በሕይወት እያለች ሁለት ልጆችን የወለድን ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 19 ቀበሌ 58 ክልል ባለቤቱ ከባንክ ገንዘብ ተበድራ ቤት ሠርታለች፡፡ ይህም ቤት የሚችና የእኔ የጋራ ቤት ሲሆን ተከሣሽ ምንም መብት ሣይኖራቸው ቤቱን ይዘው የሚገኙ ስለሆነ ለቀው እንዲያስረክቡኝና ኪራይም እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ከሣሽም ተከሣሽም የሚች ባል እንደነበሩ ተረጋግጧል ካለ በኋላ የቤቱ ግማሽ የሚስት ድርሻ ሆኖ ቀሪውን ግማሹን ደግሞ ሁለቱ የሚች ባሎች ድርሻቸው ስለሆነ በዚሁ መሠረት ከሣሽ የቤቱን ¼ኛው ይገባቸዋል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ይህ ውሣኔም በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እንደፀና ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ በኋላም አመልካች አፈፃፀም ቀጥለው በክርክሩ ሂደት የፍርድ ባለእዳ የነበሩት አቶ ተክሉ በቀለ በመሞታቸው ምክንያት ባለቤታቸው የሆኑት የአሁን ተጠሪ በፍርድ ባለእዳነት ተመዝግበው አፈፃፀሙን የያዘው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት

ፍርዱን በምን መልኩ ማስፈፀም እንዳለበት ፍርዱን ለሰጠው ችሎት ማብራሪያ ጠይቆ የቤቱ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ¼ኛው ለፍርድ ባለመብቱ በመክፈል በዚሁ መልኩ ፍርዱ እንዲፈፀም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

የፍርድ አፈፃፀሙን የያዘው ችሎትም በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ቤቶችን የቤት የገበያ ግምት የሚሰጠው የሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል ሲሆን በዚሁ መሠረትም የፍርድ አፈፃፀም መምሪያ ከዚሁ አካል ግምቱን አስቀርቦ የባለመብትን ድርሻ ¼ ከባለእዳዎች ላይ ከሚያስከፍል ውጭ ውሣኔውን ከሰጠው ፍ/ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እንዲፈፀም ከተሰጠው ትእዛዝ በመውጣት በሐራጅ ተሸጦ ለባለመብት እንዲከፈላቸው የሚያደርግበት ሥርዓት ስለሌለ የፍርድ ባለመብት በዚህ መልኩ እንዲፈፀምላቸው ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት ስለሌለው በፍርድ አፈፃፀም በኩል የተየዘውን ድርሻቸውን ይውሰዱ በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

የፍርድ ባለመብት በዚሁ ትእዛዝ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን የሥር ፍ/ቤት ትእዛዝ ጉድለት የሌለው ነው በማለት ይግባኙን ሠርሿል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታውን መርምሮ የቤቱ ወቅታዊ ዋጋ ¼ኛው ለአመልካች ይከፈላቸው ተብሎ ፍርድ በተሰጠበት ሁኔታ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ከሚመለከተው አስተዳደር ክፍል የተላከለትን ግምት መሠረት በማድረግ ፍርዱ እንዲፈፀም በማለት የሰጠው የአፈፃፀም ትእዛዝ ተጠሪ ባሉበት ለሰበር ቀርቦ ሊታይ እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡ በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተጠቀሰው ሲሆን የሰበር አቤቱታውም ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ ተመርምሯል፡፡

ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ የሰጠው የፍርድ ባለመብት /የአሁን አመልካች/ የቤቱን ወቅታዊ ዋጋ ¼ ሊከፈላቸው ይገባል በማለት

ነው፡፡ የከተማው አስተዳደር ቤቱን አስመልክቶ የሚሰጠው የዋጋ ግምትና ወቅታዊ ዋጋ ልዩነት እንዳላቸው መገመት አያዳግትም፡፡ ስለሆነም ፍ/ቤቱ የቤቱ ወቅታዊ ዋጋ ¼ኛው ለፍርድ ባለመብቱ ሊከፍል ይገባል በማለት ውሣኔ እስከሰጠ ድረስ ወቅታዊ ዋጋውን የሚወስነው በሐራጅ በሚደረግ ሽያጭ ስለሆነ በዚሁ መልኩ ፍርዱን ማስፈፀም ከውሣኔው እንደማፈንገጥ የሚቆጠር አይሆንም፡፡

በሌላ በኩልም በዚህ ችሎት ክርክር ሲደረግ ይሄው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በሌላ የአፈፃፀም መዝገብ በሐራጅ እንዲሸጥ ታዞ በብር 364,000 ሐምሌ 9 ቀን 2000 ዓ.ም እንደተሸጠ ግራ ቀኙ ወገኖች ተማምነውበታል፡፡ ይህም የቤቱ ወቅታዊ ዋጋ መሆኑን የሚያሣይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለሆነም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ከፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 373 አኳያ ተገቢነት የሌለውና የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 65156 ኀዳር 27/2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በመ.ቁ. 61890 በ16/7/2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ከቤቱ ሽያጭ ላይ ለአመልካች ሊደርሳቸው የሚገባው ¼ኛ ድርሻ ብር 91.000 /ዘጠና አንድ ሺህ/ እንዲከፈላቸው ፍርዱንም የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://chilot.me

□ስበር /መ/ቁዓ ር 37894

መጋቢት 3 ቀን 2ዐዐ1 □ም

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች፡- ወ/ሮ ጌዜ ጌቶ - ጠበቃ ሰብስቤ ባልቻ ቀርበዋል

ተጂሪ ፡- 1/ ወ/ሮ እልፍነሽ ኤርጆ - ቀርበዋል

2/ አቶ የማነ ፀጋ - ቀርበዋል

3/ .. እያሱ የማ - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

ለዚህ ችሎት ግንቦት 18 ቀን 2000 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ □ቀረበ□ □ስበር አቤቱታው ለተጠሪ ደርሶ ሐምሌ 28 ቀን 2000 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ ማመልከቻ አቅርቧል፡፡

□□ራ ቀኙን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ መደምደሚያና ለዚህም መሠረት ከሆነው የሕግ ትንታኔ አንፃር ተመርምሮ ውሣኔው ጉድለት የሌለበት ሆኖ ስለተ□ኘ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መዝገብ ቁጥር 61010 በ21/08/2ዐዐዐ □ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ 348/1/ መሠረት በአብላጫ ድምፅ ናንቷል፡፡ □□አ ፡፡ □ራ ቀኙ ኪሣራቸውን ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

የልዩነት ሀሣብ

እኔ ስሜ በአምስተኛው ተራ ቁጥር የተጠቀሰው ዳኛ አብላጫው ድምጽ በሰጠው ውሣኔ የማልስማማ በመሆኑ በሚከተለው መንገድ የተለየሁበትን ምክንያት እገልፃለሁ፡፡

1. ከሙያ አጋሮቸ የተለየሁበትን ምክንያት ከመግለጼ በፊት በመጀመሪያ በመዝገቡ የተያዘው መሠረታዊ ጭብጥና የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ በአጭሩ ማስፈር አስፈላጊ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡ ክርክሩ መጀመሪያ ፍርድ ቤት የቀረበው ከአንደኛ ተጠሪ፣ በከሣሽነት ቀርበው ከሁለተኛው ተጠሪ ጋር በሕጋዊ ጋብቻ ተሣሥረው ሲኖሩ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 18 ቁጥሩ 517 የሆነ የጋራ ቤት ያሠሩ መሆኑን ገልፀው ጋብቻው ስለፈረሰ ቤቱን እንዲያካፍለኝ በማለት ክስ አቅርበው የፌዴራል የመጀመያ ፍርድ ቤትም ቤቱ የአንደኛና የሁለተኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት ሰለሆነ እንዲካፈሉ ሰኔ 27 ቀን 1997 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የፌዴራል የመጀመያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክር የተነሣበትን ቤት የአንደኛና የሁለተኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት ነው የሚለውን ውሣኔ በመቃወም የአሁን አመልካች ቀርበው ከሁለተኛው ተጠሪ ጋር 1957 ዓ.ም በአገር ባህል ተጋብተን ጋብቻችን ፀንቶ ሲኖር ያፈራነው ቤት ስለሆነ፣ የአንደኛና የሁለተኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት ነው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ እንዲሠረዝልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ ከመጋባታቸው በፊት አንድ ክፍል ቤት ሰርተው እንደነበር ሁለተኛ ተጠሪ አንደኛ ተጠሪን ካገቡ በኋላ ሶስት ክፍል ቤት መሥራታቸውን የአመልካች ምስክሮች እንዳረጋገጡ በመተንተን ከላይ አድራሻውና ቁጥሩ የተገለፀው ሶስት ክፍል ቤት የአንደኛና የሁለተኛ ተጠሪ የጋራ

ንብረት ነው በማለት የሰጠሁትን ውሣኔ የሚያሠርዝ ወይም የሚያስለውጥ ምክንያት የለም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ቤቱ የተሠራው አንደኛ ተጠሪ እና የሁለተኛ ተጠሪ ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ እንደዚሁም በአመልካችና በሁለተኛው ተጠሪ መካከል ያለው ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች /ይግባኝ ባይ/ ቋሚ የመኖሪያ ቤት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጋምጎፋ ዞን ጨንቻ ወረዳ መሆኑ በምስክሮች የተረጋገጠ ስለሆነ ቤቱ የተሠራው ከአንደኛ ተጠሪ ጋር ሁለተኛ ተጠሪ በሚኖርበት በመሆኑ፣ አንደኛ ተጠሪ የቤቱን ግማሽ እንድትወስድና አመልካችና ሁለተኛው ተጠሪ የቤቱን ግማሽ እኩል እንዲካፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች የሁለተኛው ተጠሪ ሚስት መሆኗና ቤቱ በጋራ ያፈራነው መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የጋራ ንብረቱን እኩል የመካፈል መብቱን በሚነፍግ ሁኔታ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምላቸው የጠየቁ ሲሆን አንደኛ ተጠሪ ቤቱ መሠረት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረግሁ እኔ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አብላጫው ድምጽ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስኗል፡፡

2. በእኔ በኩል የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ መሻሻል ይገባዋል የሚል ዕምነት አለኝ፡፡ ምክንያቱም ሁለተኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር 1957 ዓ.ም በባህል መሠረት ተጋብተውና እስካሁን በጋብቻ ፀንተው እየኖሩ መሆናቸው በሥር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ሲሆን በሌላ በኩል አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ 1969 ዓ.ም ጋብቻ ፈጽመው ጋብቻቸው ፀንቶ በነበረበት ጊዜ ቤቱ የተሠራ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔዎች

ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ የምንረዳው አመልካች አንደኛ ተጠሪ ከሁለተኛ ተጠሪ ጋር ከመጋባታቸው በፊት ለአስራ ሁለት ዓመት ያህል በትዳር ወቅት ለተፈራውና ለተጠራቀመው የጋራ ንብረት አስተዋጽኦ ያደረጉ በመሆናቸው ለመረዳት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል በአዲስ አበባ ለተሠራው ቤት አንደኛ ተጠሪ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከቱ ስለመሆናቸው በቂና አሣማኝ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአመልካች ቋሚ የመኖሪያ አድራሻ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጋሞጎፋ ዞን ጨንቻ ወረዳ መሆኑንና የአንደኛ ተጠሪ ቋሚ የመኖሪያ ቦታ አዲስ አበባ ከተማ የነበረ መሆኑን በማየት አንደኛ ተጠሪ ለቤቱ ግንባታ የበለጠ አስተዋፅኦ አድርጋለች ከሚለው መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ ሆኖም ይኸ መደምደሚያ የአመልካችን የመኖሪያ ቦታ መነሻ በማድረግ የተሰጠና አጥጋቢ ማስረጃ ያለቀረበበት ነው፡፡ ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ የሚያገኙት ማናቸውም ገቢ የጋራቸው እንደሆነ የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 67 የተደነገገ ሲሆን፣ቤተሰብ በመመስረት በጋብቻ በሚኖሩበት እና በፍች ወቅት ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል መብት ያላቸው ስለመሆኑ የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 34/1/ ይደነግጋል፡፡

ከዚህ አንፃር፣ ክርክር የተነሣበትን ቤት ላይ አመልካች ከአንደኛ ተጠሪ እና ከሁለተኛ ተጠሪ እኩል መብት ያላቸው ሆኖ እያለ ያለበቂ ምክንያት አንደኛ ተጠሪ የቤቱን ሀምሣ ፐርሰንት አመልካች ደግሞ ሃያ አምስት ፐርሰንት ብቻ እንዲካፈሉ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተሻሽሎ ቤቱን አመልካች አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ ለሶስት እኩል ሊካፈሉ ይገባል ተብሎ መወሰን ነበረበት በሚል ምክንያት ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://chilot.me

የሰበር መ/ቁ. 38041

መጋቢት 22 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ታደሰ ገ/መስቀል - ወኪል በላይነሽ ሽፋው ቀረበች

ተጠሪዎች፡- 1/ ሙሉጌታ ዘካርያስ

2/ ወ/ሮ አበቡ ገበያው

3/ መሐመድ ይማም - ወኪልም ነው ቀረበ

4/ ዘውዴ ይማም

5/ ወ/ሮ ሩቅያ ይማም

6/ ወ/ሮ ዘይነባ ይማም

7/ ወ/ሮ አሚናት ይማም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአፈፃፀም ደረጃ ያለ የፍትሐብሔር ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ የጉዳዩ ታሪክ እንደሚያመለክተው በውርስ ንብረት ክፍፍል መነሻነት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በአንድ በኩል፤ ከ3 እስከ 7 ድረስ ያሉት ተጠሪዎች ደግሞ በሌላ በኩል በመሆን ክርክር ከተደረገ በኋላ፤ በወቅቱ ከሣሾች የነበሩት ከ3 እስከ 7 ድረስ ያሉት ተጠሪዎች በ1ኛ እና በ2ኛ ተጠሪዎች ላይ አስወስነው የፍርድ ባለመብት ሆነዋል፡፡ ይህን ውሣኔ መሠረት በማድረግም የአፈፃፀም መዝገብ ያስከፈቱ ሲሆን፣ በዚህን ጊዜም አመልካችንም

የአፈፃፀም ተከሣሽ አድርገውት እንደነበር እና ፍ/ቤቱ ግን አመልካች ተከሶ የተፈረደበት የፍርድ ባለእዳ አይደለም በማለት ከአፈፃፀም ክሱ ውጪ እንዳደረገው ተገንዝበናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ለ1ኛ እና ለ2ኛ ተጠሪዎች ገንዘብ አበድሮ የነበረ በመሆኑ እና የውርስ ሃብት ነው ተብሎ ተጠሪዎች የሚከራከሩበት ቤትም በመያዣ ይዞ ስለነበር ይህን የብድር እና የመያዣ ውል መነሻ በማድረግ 1ኛና 2ኛ ተጠሪዎችን በመክሰስ ቤቱን እንዲረከብ በፍ/ቤት አስወስኖአል፡፡ አመልካች ይህን ውሣኔ ያሰጠው በ1993 ዓ.ም ሲሆን፣ ከ3 እስከ 7 ድረስ የተጠቀሱት ተጠሪዎች በ1ኛና በ2ኛ ተጠሪዎች ላይ ያስወሰኑት በ1997 ዓ.ም እንደሆነ መዝገቡ ያመለክታል፡፡

አመልካች በአፈፃፀም መዝገቡ ተጣምሮ መከሰሱን እንዳየ ከ3 እስከ 7 ድረስ የተጠቀሱት ተጠሪዎች ቤቱን በተመለከተ ያሰጡት ውሣኔ መኖሩን ስላወቀ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 መሠረት መቃወሚያ አቅርቦ ክርክር ከተካሄደ በኋላ ቤቱ በመያዣ የያዘው ከመሆኑም በላይ፤ በፍርድም ለሱ ይገባል ስለተባለ ከ3 እስከ 7 ድረስ ለተጠቀሱት ተጠሪዎች ሊሰጥ አይገባም በሚል ተወስኖለታል፡፡ በዚህም በተጠሪዎች መካከል በተደረገው ክርክር መሠረት ተሰጥቶ የነበረው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 360/2/ መሠረት ተሽሮአል፡፡ ከዚህ በኋላ ከ3 እስከ 7 ድረስ የተጠቀሱት ተጠሪዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 360/2/ መሠረት የተሰጠውን ውሣኔ በመቃወም በአማራ ብ/ክ/መ/ ለደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው የነበረ ሲሆን፣ በስር ወረዳ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ጉድለት የለበትም በሚል ይግባኛቸው ሣይስተናገድ ቀርቶአል፡፡ በመጨረሻም አመልካች እና 1ኛና 2ኛ ተጠሪዎችን መልስ ሰጭ በማድረግ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረባቸው በዚህ ደረጃም ክርክሩ ተሰምቶአል፡፡ በመቀጠልም ፍ/ቤቱ በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጡትን ውሣኔዎች በመሻር አመልካች በቤቱ ላይ መብት የለውም፡፡ ቤቱ በተጠሪዎች መካከል ይከፋፈል በማለት ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ግንቦት 26 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል። አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች ጥር 24 ቀን 93 ዓ.ም በመ.ቁ. 14/93 ክርክር ባስነሣው ቤት ላይ የሰጠው ውሣኔ በይግባኝ ባልተሻረበት ሁኔታ የጠ/ፍ/ቤቱ በተጠሪዎች መካከል የነበረውን ክርክር ሲመረምር በመ.ቁ. 14/93 ላይ የተሰጠውን ውሣኔ የመሻሩን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ነው። በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል።

እንደምንመለከተው አመልካች በመ.ቁ. 14/93 ጥር 24 ቀን 93 ዓ.ም ባስወሰነው መሠረት ለክርክሩ መንስኤ በሆነው ቤት ላይ የፍርድ ባለመብት ሆኖአል። ውሣኔው የተሰጠው ከሱ ገንዘብ በተበደሩት እና ቤቱንም በመያዣ በሰጡት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ላይ በመሠረተው ክስ መነሻነት ነው። ይህ ፍርድ ለየትኛውም ፍ/ቤት በይግባኝ ቀርቦ አልተሻረም። ከ3 እስከ 7 ድረስ የተጠቀሱት ተጠሪዎች ይህን አመልካች በመክሰስ በቤቱ ላይ መብት አላገኙም። ከዚህ የተነሣም አመልካች ቤቱን ያስረክባቸው ዘንድ የሚያስገድዱበት ምንም የሕግ ምክንያት የለም። አመልካች በቤቱ ላይ ያገኘው በፍርድ ላይ የተመሠረተ የባለቤትነት መብት በተመሣሣይ ሁኔታ በፍርድ ሃይል እስካልተነሣ ድረስ ምን ጊዜም የቤቱ ባለቤት ሆኖ የሚቀረው አመልካቹ ነው።

የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በስር ወረዳ ፍ/ቤትም ሆነ በከፍተኛ ፍ/ቤት በተሰጠው አመልካችን የቤቱ ባለቤት ባደረገው ውሣኔ ላይ ይግባኝ አልቀረበለትም። ቤቱ የአመልካች አይሆንም በማለት የወሰነው በይግባኝ ያልቀረበለትን ውሣኔ ተፈፃሚነት የሚኖረው ውሣኔ አይደለም የሚል ትችት በመስጠት እንደሆነ ከውሣኔው ይዘት ለመገንዘብ ችለናል። በመሠረቱ በሕግ አግባብ በፍ/ቤት የተሰጠን ውሣኔ የሞራልን ወይም የሕሊናን አስተሳሰብ መሠረት በማድረግ ዋጋ አልባ ሆኖ እንዲቀር ማድረግ

በየትኛውም መለኪያ ተቀባይነት የሚኖረው አይደለም፡፡ በተያዘው ጉዳይ እንደሚታየው 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በክስ እንደሌሎቹ ተጠሪዎች በቤቱ ላይ የውርስ መብት እንደነበራቸው ተመልክተዋል፡፡ ቤቱን ለብድር በመያዣነት ለአመልካች የሰጡትም በእነሱ እጅ ስለነበረ እንደሆነ ይገመታል፡፡ ለምን እነሱ ብቻቸውን በመያዣነት ሰጡ ብሎ መጠየቁም አግባብ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ከዚህ ሁሉ በፊት አመልካች ቤቱን በፍርድ የሱ እንዲሆን አድርጓል፡፡ በመሆኑም ሌሎችም የውርስ መበት አላቸው ስለተባለ ብቻ ያለምንም ሕጋዊ ምክንያት ፍርዱ ተፈፃሚ እንዳይሆን ወይም ማምከን አይቻልም፡፡ ሲጠቃለል የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 311/2000 ግንቦት 12 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡ የደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጡአቸው ትእዛዝና ውሣኔ ፀንተዋል፡፡
2. አመልካች ጥር 24 ቀን 93 ዓ.ም በመ.ቁ. 14/93 በተሰጠው ውሣኔ በቤቱ ላይ ባለመብት ስለሆነ ለተጠሪዎች ሊያስረክብ አይገደድም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፣፣

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 38126

መጋቢት 22 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ዲያቆን ኃ/ጊዮርጊስ ወንድም ሲያምረኝ ቀረቡ

ተጠሪ፡- እነ ወ/ሮ የሺ ተፈሪ (2 ሰዎች) ቀረቡ

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፊ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው። በዚህ ፍ/ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ናቸው። በክሣቸው ከአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ጋር ባልና ሚስት ሆነው በጋራ የሰሩት የእሣቸው ፈቃድ ሣይኖር 2ኛ ተጠሪ ለአመልካች መስጠታቸውን በመግለጽ የሺያጩ ውል ከተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ጋር የሚቃረንና ሕጉ የሚጠይቀውን ፎርማሊቲ ያልተከተለ በመሆኑ ፈራሽ ነው እንዲባልላቸው ጠይቀዋል። ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም የሺያጭ ውሉ በፍ/ህ/ቁ. 1723(1) መሰረት በህግ የሚጠይቀውን የአፃፃፍ ስርአት አልተከተለም በማለት ውሉ እንዲፈረስ ውሣኔ ሰጠ። አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፊ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ መልስ ሰጪን መጥራት ሣያስፈልግ ይግባኙን ሰርዞታል።

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሣኔ በመቃወም ነው። የአመልካች ዋነኛ ቅሬታ የስር ከሣሽ ያቀረቡት ክስ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አ/ቁ. 213/92 አንቀጽ 69/2/ መሰረት በይርጋ የታገደ ነው የሚል ነው። ይህ ችሎትም የአመልካች አቤቱታ

ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊታይ ይገባል በማለቱ ተጠሪዎች ቀርበው ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ አግባብ ካለው የህግ ድንጋጌ ጋር እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለጸው በስር ፍ/ቤት ከሳሽ የነበሩት 1ኛ ተጠሪ ክስ ያቀረቡት ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በጋብቻ ውስጥ ያፈሩት የጋራ ቤታቸውን 2ኛ ተጠሪ ያለ እሳቸው ፈቃድ ለአመልካች ከመሸጣቸውም በላይ ውሉ በሕግ የተመለከተውን የአፃፃፍ ስርአት ስለማያሟላ እንዲፈርስላቸው ነው፡፡ አመልካች የቀረበው ክስ በይርጋ ይታገዳል የሚልና ሌላም መቃወሚያ እንዲሁም ለዋናው ጉዳይ በአማራጭ ሙሉ መልስ ሰጥተዋል፡፡ በመሆኑም አመልካች ያቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ በቅድሚያ ሊታይ ይገባል፡፡

ከመዝገቡ ላይ በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መሐከል የሽያጭ ውል የተደረገው ጎዳር 1 ቀን 1995 መሆኑና የስር ከሣሽ ወይም የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ክስ የመሰረቱት በ09/08/1999 ዓ.ም መሆኑን ተረድተናል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ክሱን የተቃወሙት ውል የተደረገበት ቤት ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያፈሩት የጋራ ንብረት በመሆኑ ነው፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 68 ፊደል “ሀ” ስር የጋራ የሆነውን የማይንቀሣቀስ ንብረት ለመሸጥ የሁለቱም ተጋቢዎች ስምምነት አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ስምምነት ሣይኖር የተደረገ ሽያጭ ውጤቱ ምን እንደሆነ በዚህ ህግ አንቀጽ 69 ስር ተቀምጧል አንደኛው ተጋቢ በሌላኛው ተጋቢ ስምምነት ሣይኖር የጋራ የሆነውን የማይንቀሣቀስ ንብረት የሸጠ እንደሆነ ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢ ውሉ እንዲፈርስ ሲጠይቅ እንደሚችልና ፍ/ቤቱ ውሉን ማፍረስ እንደሚችል ተገልጸአል፡፡

በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪና 2ኛ ተጠሪ በጋብቻ ጊዜ ያፈሩት የጋራ ቤት የ1ኛ ተጠሪ ፈቃድ ሣይኖር ተሸጦ ከሆነ ተጠሪዋ ውሉ እንዲፈረስ ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡ በሌላ በኩል ግን ግዴታው እንዲፈርስ የሚቀርበው ጥያቄ ጠያቂው ወገን ግዴታው

መገባቱን ከአወቀበት ቀን ጀምሮ ከ6 ወር በኋላ በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ግዴታው ከተገባ ከሁለት ዓመት በኋላ ሊቀርብ እንደማይችል በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 69/2/ ስር ተደንግጓል፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለፀው በ2ኛ ተጠሪና በአመልካች መሐከል የቤት ሺያጭ ውል የተደረገው 01/03/95 ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ክስ ያቀረቡት ደግሞ በ09/08/99 ከአራት አመት በኋላ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን የይርጋ ክርክር ውድቅ ያደረገው የስር 1ኛ ተከሣሽ ከሣሽ በሆኑበት መዝገብ 1ኛ ተጠሪ ተከሣሽ ሆነው ቀርበው ተከራክረው ከተወሰነ በኋላ ፍ/ቤቱ የ1ኛ ተጠሪን ክስ የማቅረብ መብት የጠበቀላቸው በመሆኑና ይህም ውሣኔ ከተሰጠ ጀምሮ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ክሱ በመቅረቡ ይርጋው ተቀባይነት የለውም በማለት ነው፡፡ አንድ ክስ ለማቅረብ በህጉ የተመለከተው በይርጋ ጊዜ ካለፈ በኋላ ክስ ማቅረብ የማይቻል ቢሆንም ነገር ግን አሁንም ህጉ ለይቶ ባስቀመጣቸው ምክንያቶች የይርጋው ጊዜ ሊቋረጥ እንደሚችልና አዲስ የይርጋ ዘመን መቆጠር እንደሚጀምር የፍ/ሕ/ቁ. 1852/1/ ያመለክታል፡፡ ወይም በፍ/ህ/ቁ. 1853 ስር የተመለከተው ሁኔታ ሲያጋጥም ፍ/ቤቱ የይርጋን መቃወሚያ አልቀበልም ለማለት ይችላል፡፡ ይርጋ የሚቋረጥባቸው ምክንያቶች የሚባሉት የባለእዳው እዳው ማመኑ፣ ወለድ ወይም ከእዳው ላይ ከፊሉን መክፈሉ፣ መያዣ ወይም ዋስ መስጠቱ ወይም ደግሞ ባለገንዘቡ መብቱ እንዲታወቅለት በፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ባለእዳውን ማሣወቁ መሆናቸው ከፍ/ህ/ቁ. 1851(1)(2) መረዳት ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የሺያጭ ውሉ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ 1ኛ ተጠሪ ክስ እስካቀረቡበት ጊዜ ድረስ 4 አመት ያለፈው በመሆኑ ክሣቸው በተሻሻለው ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 69/2/ መሰረት በይርጋ ቀሪ ሆኗል፡፡ በዚህ አራት አመት ውስጥ የይርጋውን የሚያቋርጡ ሁኔታዎች (በህጉ በተመለከቱት አይነት) ስለማጋጠማቸው የቀረበ ነገር የለም፡፡ ፍ/ቤቱ በጠቀሰው መዝገብ ላይ የ1ኛ ተጠሪ ክስ የማቅረብ መብት ያላቸው

መሆኑ መገለጽ የይርጋውን ጊዜ ለማቋረጥ የሚበቃ ምክንያት አይሆንም፡፡ በሌላ በኩል በተጠቀሰው መዝገብ 1ኛ ተጠሪ ተከሣሽ እንጂ ከሣሽ ለመሆናቸው መብታቸው እንዲታወቅላቸው በፍ/ቤት ክስ አቅርበዋል ሊባል የሚችሉ ባለመሆናቸው በፍ/ህ/ቁ. 1851/ለ/ መሰረት የይርጋው ጊዜ ተቋርጧል ለማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም ውሉ ከተደረገ ከ4 አመት በኋላ የቀረበው ክስ በይርጋ ሊቋረጥ ሲገባ የአመልካችን የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ ማደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት ብለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 58635 በ12/09/2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ እና የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 44809 በ27/11/99 የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የከሣሽ የዳኝነት ጥያቄ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ቁጥር 69/2/ መሰረት በይርጋ ይቋረጣል ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን